# በዓለም የተታለለች፡ ቤተክርስትያን

ልጁ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ እና፡ በክርስቶስ በኩልም ሁሉን በነጻ ሰጥቶናል። ጌታ ሆይ፡ ስለ ተሰጠን ጸጋ፡ እጅግ እናመሰግንሃለን ኢየሱስ በቀራንዮ ለእኛ በሰጠን በዚህ ታላቅ መስዋዕት፣ ሞገስ እንዲሆንልን ሕብረትም እንድናደርግ ከአንተ ዘንድ አስታርቆናልና፣ የተጻፈውን በማወቅ መጽናናት ይሆንልን ዘንድ፦ “በእኔ ብትኖሩ፡ ቃሎቼም በእናንተ ቢኖሩ፡ የምትወዱትን ሁሉ ለምኑ፡ ይሆንላችኋል ብሎናል።” አሁንም፡ ስለዚህ ነገር እናመሰግናለን፡ ደግሞም ባለን አቅም ሁሉ እንድናምን እምነት እንድትሰጠን ጸለይን።

2 ጌታ ሆይ፡ የቀኑን የትኛው ውጣውረድ፡ ወደ ጎን ብለን፣ ከጽዳት ሰራተኛው እስከ ፓስተሩ ሁላችንም፡ የኑሮን ሐሳብ ሁሉ ትተን፣ መንፈስ ቅዱስ ሲናገር ለመስማት፡ አሁን ስንጠባበቅ፡ በአእምሮአችን አንዳች ነገር አይኑር፣ ይህም አንድ ላይ በመሆናችን፡ ስለ አንተ አብዝተን ለማወቅና፡ እንዲሁም መልካም ነገርን እንፈጽም ዘንድ ነው። ጌታ ሆይ፡ በዚህ ሞቃታማው ቀን፡ የመጣንበት ምክንያት ይህ ነውና። በህያው ቃልህ ተናገረን፡ ህያው ቃልህ አብሮን ይሁን ከእኛም ጋር ይኑር፣ ዓለምን ስለ መምሰል፡ መቀረጽ እና መሰራት ሳይሆን፡ በመንፈሳችን ግን በመታደስ፣ ወደ እግዚአብሄር ልጅ ምሳሌ እንድንለወጥ ነው። ኦህ፡ ይህን ስናስብ ልባችን ይዘላል፡ ደስታም በነፍሳችን ውስጥ ይፈሳል፣ የእግዚአብሄር ወንድ እና ሴት ልጆች ተብለን መጠራት እንድምንችል ሰናውቅ። አሕዛብ እና መንግስታት ከእግራችን በታች በሚንቀጠቀጡበት፡ ወደ ዳግም ምጽአቱ ደጅ ደርሰናል፣ የአለም አሸንክታቦች ሁሉ የሚጠፉበት፡ እኛ ግን አንድ ቀን መጥቶ ወደ መንግስትም እንደሚወስደን ይህን አውቀን ፈጽማ ወደ ማትሸነፍ፡ ወይም፡ ፍጻሜ ወደ ሌለባት ይወስደናል። አሁንም የዚያች መንግስት——ተጠሪዎች መሆናችንን ሰናስብ! አምላክ ሆይ፡ ዛሬ በመንፈስ ቅዱስና፡ በቃሉ ውሃ——በማጠብ፡ ልቦቻችንን እና ጆሮአችንን ግረዝ። ስለ ስምህ እና ስለ ክብርህ ብለን ለመንን። አሜን።

3 ዛሬ ማለዳ ልናገር የፈለግኩት ርዕስ አለ። ምክንያቱ፡ የፈውስ ፕሮግራም የሚኖር ከሆነ ለየት ባለ ርዕስ ጉዳይ መናገር ፈልጌአለሁ፣ ይሁን እንጂ የጸሎት ካርዶች ሰምንት ሰዓት እስከ ሰምንት-ከሰላሳ ወይም ዘጠኝ ሰዓት ድረስ፡ ይታደላል ብለን አውጀን ነበርን። እኔም... ቢሉ ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት ወደ ቤት ሲመጣ አንድም ሰው ወደዚህ አለመምጣቱ ነገረኝ፣ ሰለዚህ የጸሎት ካርዶችን አልሰጠም። ሰለዚህ... ይህ ርዕስ፡ ቤተክርስትያንን ለመምከር ብጠቀምበት ብየ አሰብኩ። እና **በዓለም የተታለለች፡ ቤተክርስትያን** በሚል ርዕስ ጉዳይ፤ መናገር ፈልጌአለሁ። ከመጽሐፈ መሳፍንት፡ 16ኛው ምዕራፍ፡ ከ10ኛው ቁጥር ጀምሬ ትንሽ ማንበብ እፈልጋለሁ።

**ደሊላም ሶምሶንን፡ እነሆ፡ አታለልኸኝ፡ የነገርኸኝም ሀሰት ነው፤ አሁንም የምትታሰርበት** ምን እንደ ሆነ፥ **እባክህ፥ ንገረኝ አለችው።**

**እርሱም ሥራ ባልተሠራበት፡ በአዲስ ገመድ** ቢያስሩኝ፣ **እደክማለሁ፥ እንደ ሌላም ሰው እሆናለሁ አላት።**

ደሊላም አዲስ ገመድ ወስዳ በእርሱ አሰረችው፡ እርሰዋም፡ ሶምሶን ሆይ፥ ፍልስጥኤማውያን መጡብህ አለችው። በጓዳዋም የተደበቁ ሰዎች ተቀምጠው ነበር። ገመዱንም ከክንዱ እንደ ፈትል በጣጠሰው።

ደሊላም ሶምሶንን፡ እስከ አሁን ድረስ አታለልኸኝ፡ የነገርኸኝም ሐሰት ነው፤ የምትታሰርበት ምን እንደ ሆነ ንገረኝ አለችው። እርሱም፡ የራሴን ጠጕር ሰባቱን ጕንጕን... ከድር ጋር፡ ብትጐነጕኚው።

በችካልም ቸከለችውና፡ ሶምሶን ሆይ፥ ፍልስጥኤማውያን መጡብህ፡ አለችው። ከእንቅልፉም ነቃ፡ ችካሉንም ከነቆንዳላው፡ ድሩንም ነቀለ።

እርሰዋም፡ አንተ፡ እወድድሻለሁ እንዴት ትለኛለህ፡ ልብህ ከእኔ ጋር አይደለም? ስታታልለኝ ይህ ሦስተኛ ጊዜህ ነው፥ ታላቅ ኃይልህም በምን እንደ ሆነ... አልነገርኸኝም አለችው፡ ታላቅ ኃይልህም በምን እንደ ሆነ አልነገርኸኝም አለችው።

ዕለት ዕለትም፡ በቃልዋ ነዘነዘችው አስቸገረችውም፥ ወተወተችው፡ ነፍሱም እስከ ሞት ድረስ ተጨነቀች፣

እርሱም፡ የልቡን ሁሉ አጫወታት፡ በራሴ ላይ ምላጭ አልደረሰም አላት፣ ከእናቴ ማኅፀን ጀምሬ ለእግዚአብሄር ናዝራዊ ነኝና፣ ከተላጨሁ፡ ሀይሌ ከእኔ ይሄዳል፡ እንደ ሌላም ሰውም እደክማለሁ፡ ብሎ ገለጠላት።

ደሊላም የልቡን ሁሉ እንደ ገለጠላት ባየች ጊዜ፤ የልቡን ሁሉ ገልጦልኛልና፡ ይህን ጊዜ ደግሞ ኑ፡ ብላ ላከችና... የፍልስጥኤማውያንን መኳንንት፡ ጠራች። የፍልስጥኤማውያን መኳንንትም ብሩን በእጃቸው ይዘው፡ ወደ እርሰዋ መጡ፡ ወይም ገንዘቡን ወደ እጇ አመጡ።

እርሰዋም በጉልበትዋ ላይ አስተኛችው፡ አንድ ሰውም ጠራች፣ እርሱም ሰባቱን የራሱን ጕንጕን ላጨው፡ ልታዋርደውም... ጀመረች፡ ኃይሉም ከእርሱ ሄደ።

እርሰዋም፡ ሶምሶን ሆይ፡ ፍልስጥኤማውያን መጡብህ አለችው። ከእንቅልፉም ነቅቶ፡ እወጣለሁ፡ እንደ ወትሮውም ጊዜ አደርጋለሁ፡ አለ። ነገር ግን እግዚአብሔር ከእርሱ እንደ ተለየው አላወቀም።

4 አሁንም ለዚህ ርዕስ፡ የሚሆነን ይዘት ባነብ ደስ ይለኛል፡ ከራእይ መጽሐፍ፡ 2ኛው ምዕራፍ ላይ፡ ከ21ኛው ቁጥር ጀምሮ እስከ 23ኛው ቁጥር ባለው ላይ።

ንስሐም እንድትገባ ጊዜ ሰጠኋት ከዝሙትዋም፡ ንስሐ እንድትገባ አልወደደችም።

**እነሆ፥ በአልጋ ላይ እጥላታለሁ፡ ከእርሰዋም ጋር** የሚያመነዝሩትን፤ **ከሥራዋ ንሰሐ ባይገቡ በታላቅ መከራ እጥላቸዋለሁ።**

**ልጆችዋንም በሞት እገድላቸዋለሁ፤ አብያተ ክርስቲያናትም ሁሉ ኵላሊትንና ልብን የምመረምር እኔ እንደ ሆንሁ ያውቃሉ፥ ለእያንዳንዳችሁም እንደ ሥራችሁ እሰጣችኋለሁ።**

ጌታ በቃሉ መነበብ ላይ በረከቱን ይጨምርበት።

5 ሳምሶን፡ እንደ ቤተክርስትያን ታላቅ ጉዳይ፡ አጀማመሩ ያምራል። በትክክለኛ አቅጣጫ ጀመረ። ጀመረና፡ ታላቅ እና ገናናም ሰው ተባለ። ቃሉን እየጠበቀ፡ ትዕዛዛቱንም እያደረገ፡ ጌታን ለማገልገል መውጣት ጀመረ። ይህ ደግሞ በተወሰነ መልኩ ቤተክርስትያን ነበረች። መመላለስ ጀመረ፡ በዓለምኛ አገላለጽ፡ እንደሚባለው፡ ትክክለኛ አካሄድ ጀመረ። የጌታን ትዕዛዛት መጠበቅ ጀመረ። ሳምሶን ጌታን እስከተከተለው ድረስ፡ ጌታ ሳምሶንን ይጠቀምበታል።

6 ምክንያቱ፡ የሚከተለው ማንም ሰው ካገኘ እግዚአብሄር ይጠብቀዋል ይጠቀምበታል፡ የእግዚአብሄር ስራ ይህ ነውና። ነገር ግን፡ ከእግዚአብሄር ነገሮች ዞር ባልን ጊዜ፡ ከዚያ በኋላ እግዚአብሄር አይጠቀምብንም። ከእግዚአብሔር ትእዛዛት ጋር በጽናት ሰንኳዝ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ገጾች ውስጥ ስንኖር እና በተጻፈው ቃል ሰናመልክ፣ በመንፈስ እና በቃሉ እውነት እርሱን ሰናመልከው፣ ከዚያ እግዚአብሔር ማንኛውንም ግለሰብ ሊጠቀም ይችላል። ነገር ግን ነገሮች ተከትለው ዞር ለማለት ሌላ አመለካከት ሲይዙ፣ ከዚያ በኋላ እግዚአብሔር ያንን ሰው አይጠቀምበትም።

7 ስለዚህ፡ ሳምሶን የዛሬዋን ቤተክርስትያን ለመመሰል—እጅግ ድንቅ ምሳሌ ነው። ቤተክርስትያን በጀመረች ጊዜ፡ በጌታ ትእዛዛት በትጋት ስለተመላለሰች፣ እግዚአብሔር ቤተክርስቲያኑን ሊጠቀምባት ችሏል፣ ፍርዱን ሁሉና ሕግጋጋቱን ጠብቃለች፣ ትዕዛዛቱንም ሁሉ ፈጽማለች። እግዚአብሄርም ከቤተክርስትያን ጋር ነበረ። ነገር ግን በቤተክርስቲያኑ ውስጥ ደካማ ጎን ያለ ይመስላል።

8 አስታውሱ፡ ያለነው በጦር አውድማ ላይ እንጂ፡ ሽርሽር አይደለም። ብዙ ሰዎች ክርስትያን ሲሆኑ ከእነሱ የሚጠበቀው ይህ ብቻ ነው፣ ለዘለአለም አልጋ በአልጋ የሚያደርግላቸው፣ ክርስትያን ከሆኑ በኋላ ነገር ሁሉ ቀላል የሚሆን ይመስላቸዋል። በፍጹም እንዲህ አይነት ሐሳብ አይኑራችሁ። ገድልን፡ ለመጋደል ክርትያን ሆኛለሁና፡ መልካሙን የእምነት ገድል ለመጋደል። በጦር ሜዳ ለመሰለፍ፡ ክርሰትያን ሆንኩኝ። የክርስትያን ሰራዊት ነን፣ ስለዚህ መሰልጠን እና ማደግ አለብን፣ የጠላትን ሰልቶች ሁሉ ማወቅ አለብን፣ እንዴት መመሸግ እንዳለብን ለማወቅ፣ ሰልፉን እንዴት—መሰለፍ እንዳለብን ለመረዳት። ይህ ማድረግ የሚቻለን መንፈስ ቅዱስ ሊገልጥልን በወደደ ጊዜ ብቻ ነው። ወደ ሰልፍ ሰንወጣ፡ ሌሎች አሕዛብ የሚነግሩንን፣ ሐሳቦቻቸውን መቀበል አይገባንም። ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በሚመራን አቅጣጫና፣ እሱ በሚሰጠን ሐሳብ፣ የራሳችን አቋም እንያዝ፣ የክርሰትያን ሰራዊት ዋና አዛዥ እርሱ ነውና።

9 ሳምሶን መቅለስለስ እስኪጀምር (ምንድነው የሚባለው) መቅለስለስ እስኪጀምር ድረስ፡ መልካም አድርጓል፣ ታላቅ ሰው ነበር፣ ሰፍራውን ለቆ መሄድ እስኪጀምር ድረስ። ቤተክርስትያንም በትክክል ተጓዘች፣ ሰፍራቸው መተው እስኪጀምሩ ድረስ ሁለቱም ትክክል ነበሩ። ሳምሶን መዳራት ጀመረ። የሚዳራቸው ሴቶች ግን እስራኤላውያን አልነበሩም፣ ከፍልስጥኤም ሴቶች ጋር መቀለድ ጀመረ።

10 የቤተክርስትያን ድርጊትም በመጠኑም ቢሆን ይሄንን ይመስላል። ፍቅርን ማድረግ በፍጹም ከወገኖቹ ጋር አልጀመረም፡ የማያምንቱን ተከተለ ከማያምኑት ጋራ መዳራት ጀመረ። እዚህ ጋር ነው የምንሰተው፣ ዋና እና ትልቁ ስሕተት፣ ቤተክርስትያን ትክክል ያልሆኑ ነገሮች መፈጸም ስትጀምር ነው። እንደ ሳምሶን፡ መጥፎ ወዳጅነትን፡ ትቀጥልበታለች።

11 ሳምሶን'ኮ፡ ከጌታ ህዝብ ጋር በወዳጅነት በነበረ ጊዜ፡ መልካምን አድርጓል። ነገር ግን ከክፉ ወዳጆች ጋር መዳራት የጀመረለታ፡ ችግር ውስጥ ገባ።

12 የቤተክርስቲያን ጉዳይም እንዲሁ ነው። ቤተክርስትያን መንፈስ ቅዱስ በሚመራት ምሪት ዘወትር በትሕትና ስትከተለው፣ እግዚአብሄር ይባርካቸዋል፣ ምልክቶች ድንቆች እና ተአምራቶች ቤተክርስትያኒቱን ይከተሏታል። ከዓለም ጋር መጥፎ ወዳጅነት፡ ስትጀምር ግን! የሚሆንባት አንደኛ ክፉ ነገር፡ እና በመጀምርያ የሚሆን ክፉ ነገር፣ መደራጀት ይጀመራል፣ ከሌሎች አማኞች ጋር የነበረው ህብረት ይቀራል፣ ምክንያቱ አሕዛብ እየተደራጁ መሆናቸውን ስለሚገነዘቡ። ይህ ታላቅ ወንጌል ግን ለአንዲት አገር ወይም ለአንድ ህዝብ የተበረከተ አይደለም። ለሁሉ የተሰጠ ነው "የተጠማ ቢኖር፣ ይምጣ፡" ለአገር፣ ለወገኖች፣ ለቋንቋዎች፣ እና ህዝብ። እግዚአብሔር ፈጽሞ ድንበር እንድናሰምር አይፈልገንም።

13 ሰዎች ግን በንጽጽር፣ ወይም በኩረጃ፣ እንደ—ዓለም በመጓዝ፣ መመሳሰል ይፈልጋሉ፣ እነሱ የሚያደርጉት ነገር ስኬታማ ያደረጋቸው መንገድ፣ ስኬት አለው ይላሉ። ዓለም በሚጠቀምበት የትኛውም አሰራር ስኬታማ እንሆንም። ስኬታማ የምንሆንበት ብቸኛ መንገድ የእግዚአብሄር ስርዓቶችን እና የእሱ አሰራር በመከተል ብቻ ነው። ዓለምን ንድፍ አርገን፡ ፈጽሞ አይሳካልንም። የሲጋራ አምራች ኩባንያ ቴሌቪዥን በመጠቀም ታላቅ ስኬት ካስመዘገበ፣ የቢራ እና የዊስኪ ጋጋታ ታላቁ ስኬታቸው በቴሌቪዥን ድርሻ ካስመዘገቡ፣ ቤተክርስትያን ስኬትዋን የምታስመዘግብበት ምልክቱ ቴሌቪዥን ነው ማለት አይደለም። ቤተክርትስያን ስኬቷ የሚገኘው የእግዚአብሄር ሀይል በሆነው፣ በወንጌል ስብከት ውስጥ ነው፣ እንዲሁም በመንፈስ መገለጫዎች ጭምር። ቴሌቪዥኝ ለሲጋራ ኩባንያ—እና ለሌሎች ኩባንያዎች **እንዲህ-እና-እንዲያ** ስላደረገላቸው ማለት አንችልም! ከእነዚያ ማሕበረሰብ ጋር ተነጻጸሩ የሚለን ቅዱስ ቃል የለም። እስከ ፈጸምነው ድረስ ግን፡ ምናልባት ብዙ ህዝብ ልናስከትልበት እንችል ይሆናል፡ እግዚአብሄር ግን ይህን እንድንሰራ አልቀባንም። ሁላችንም ህብረ ቀለም፣ አንድ ላይ ብንበርር ብለን ስለምናስብ፣ ታላላቅ ድርጅቶች ሆነን፣ ልዩ ልዩ ህብር ያላቸው ታላላቅ ነገሮች ሲሆኑ፣ ስኬት ካልነው። በየቀኑ ባለንበት እየሞትን ነው፡ መንፈሳዊ አነጋገር! ዛሬ አሰር-ሚልየን ጠንካሮች አብረን ቆመን፡ መንፈስ ቅዱስ ከእኛ ጋር ከሌለ፡ መንፈስ

ቅዱስ ኢብርን ሆኖ አሰር ሰዎች የተሻለ መሰራት እንችላለን። ከዓለም ጋር መነጻጸር አንችልም።

14 እና የመጀመርያ የሆነው ነገር፡ ቤተክርስትያኒቱ፡ መደራጀት መጀመራቸው ነው። የመጀመርያዋ ድርጅት ካቶሊክ ቤተ እምነት ነበረች፣ ከሷ ቀጥላ ሉተራን ቤተ እምነት መጣች። ድርጅት ለመሆ በካቶሊክ ቤተክርስትያን በተሰበሰቡ ጊዜ፡ አንድ ቀን ድምጽ ሆነ፦ "ሶምሶን ሆይ፡ ፍልስጥኤማውያን መጡብህ፡" ሳምሶንም የካቶሊክ ቤተክርስትያን የእሰራት ገመድን በጣጠሰ፣ እና ድርጅቶቹ ጋር፡ ማርቲን ሉተር ወጣ።

15 ከዚያ በኋላ ደሊላ እንዳደረገችው፡ ቤተክርስትያኒቱን በሌላ ገመድ አሰሯት። እና እንዲህ ጀመሩ... እግዚአብሄር-ከጠራቸው፣ በመንፈስ ቅዱስ ከተጠሩ ሰዎች ይልቅ፣ ምናልባት ሀሁ ላያውቁ ይችላሉ፡ ክርስቶስን ግን ያውቁታል። ከዚያ በኋላ ቤተክርስትያን፡ ፖለቲካ ተናጋሪዎች በመከተል፣ ቄንጠኛ እና ፋሽን ተከታይ ትሆናለች። ሰባኪዎቻቸውን "ዶክትሬት ዲግሪ" መስጠት ነበረባቸው፡ ሁሉንም የስነመለኮት ዶክተር መሆን አለባቸው። ቤተክርስትያኒቱን ለማሰር ሌላኛው ገመድ ይህ ነበር። ወንዶች ለመማር ይሄዳሉ እያንዳንዳቸው ትምህርት ቤቶች የተሻለ ምሁር ለማፍራት ይጥራሉ፣ ቤተክርስትያናቸው እንዲመኩ፦ "ፓስተራችን በስነመለኮት ዶክትሬት አለው እንዲሉ።" ከዛስ ምን ያደርጋሉ? አንደኛው ከሌላ የተሻለ ዕውቀት ለመከመር ይጣጣራሉ። እንግዲህ፡ ይህ በእግዚአብሄር ፊት ምንም ትርጉም የለውም።

16 ማንም ሰው እግዚአብሔርን ለማስደሰት ዓለማዊ እውቀቱን ለመጠቀም መሞከር በፍፁም አያስፈልገውም። በእግዚአብሔር ፊት ርኩሰት ነው! በአለማዊ ምኞት እና እውቀት እግዚአብሔርን በጭራሽ አታስደስቱትም፣ ምክንያቱም "ለእግዚአብሔር ጥል ነው፣" ይላል ቅዱስ ቃል። አያረገውም።

17 እያንዳንዳቸው ዕውቀትን ሁሉ ለመከመር ይጥራሉ። እንዴት ማድረግ እንዳለባቸው እና ማለት የሚገባቸው ቃላት ብቻ ያውቃሉ፣ በሀይል የተለቀቀ መንፈስ ቅዱስ መልዕክት ይልቅ፤ ተራ የፖለቲካ ንግግር ይሆናል በሰው ልብ ዘልቆ ሐጥያቱን ከሚመረምር ይልቅ። በፖለቲካ ንግግሮች የሰለጠኑ ናቸው፡ እኛ ደግሞ ይሄ አያስፈልገንም። ጳውሎስ ሲናገር፦ "ቃል... ወይም፡ በወንጌል፡ ቃል ብቻ፡ ወደ እኛ አልመጣም፣ በኃይልና በመንፈስ ቅዱስ በብዙ መረዳትም እንጂ።" ይህም ወንጌልን፡ የመንፈስ ቅዱስን ኃይል እንዲገልጥ ያደርገዋል! እነዚህ ሰዎች ግን ወደ ትምህርት ቤቶች በመሄድ በሰው ፊት እንዴት መቆም እንደሚገባቸው፣ ብዙ ትምህርቶችን ይማራሉ፣ እራሳቸውን እንዴት ማቅረብ እንደሚገባቸው፣ እንዴት እንደሚለብሱ እንዴት እንደሚንቀሳቀሱ፣ የተሳሳተ ሰዋሰው በፍጹም መጠቀም እንደሌለባቸው ይሰለጥናሉ። አሁን ይህ ሁሉ፡ ለፖለቲካ ንግግር ጥሩ ነው፣ ነገር ግን የኛ ፍላጎት እንደበተ ርቱዕ የሰው ቃላት መስማት አይደለም። ጳውሎስ ሲናገር "እኔ የምሰብከው ወንጌል በእንዲህ መልኩ አልመጣም፣ ነገር ግን በመንፈስ ቅዱስ በመታደስ እና—በመገለጥ ሐይሉ እንጂ ብሏል።" ጥበባችሁ፣ ወይ እምነታችሁ በሰው ጥበብ እንዳይሆን፣ በተቀመመ አንደበት አልመጣም። የመጣው ግን በተነሳው ክርስቶስ ኃይልና በመንፈስ ቅዱስ በመገለጥ ነው። ወንጌል ማለት፦ "በትንሳኤው ኃይል እሱን ማወቅ" ነው።

18 እያንዳንዱ የእምነት ተቋም፡ እያንዳንዱ፣ አንዱ ከሌላኛው እንደሚሻል ይቆጥራል። ሜተዲስታውያን፡ “ከሁሉ የሚበልጥ ሰው አለን” ይላሉ። ባብቲስቶች፣ እና ቸርች ኦፍ ክራይስት፣ ወዘተ፡ ሁሉንም፡- “እኛ እንበልጣለን። እኛ፡ የኛ—ሰዎች፡ ተራ ሰዎችን ወደ ወንጌል ሰብከት አንልክም።” በእጅ-ተለቅመው የተመረጡት እንጂ ይላሉ። (እምላክ ሆይ፣ ምሕረት አርግልን!) በእጅ-የተለቀሙ፡ ማለት በአንድ አንድ ዶክትሪኖች የታመነ-ዶክመንት የያዙ ከሆኑ፣ ከዛ ቤተክርስትያን ውስጥ ያስገቧቸዋል ማለት ነው። ጌታ በጭራሽ አይዳስሳቸውም። እኔ የምፈልገው፡ እግዚአብሄር ያሳደገው የመንፈስ ቅዱስ እጅ-የመረጠው ሰው እንዲሰብከኝ ነው፣ በሰው ይሁን በድርጅት የተመረጠ አልፈልግም።

19 እውቀት ሁሉ! “ኦህ፡ ሙሉ ለሙሉ እናውቀዋለን፣” ይላሉ፣ አንዳንዶቹ’ኮ የመንፈስ ቅዱስን የመጀመሪያ ፊደል እንኳን አያውቁትም። ይክዱታል።

20 የዛሬ አስር ዓመት፣ በካሊፎርኒያ ያነበብኳት ትንሽ መጽሐፍ ያስታውሰኛል። ከታዋቂ የመጻሕፍት መደብር አግኝቼአት ነው። ደራሲው ማን እንደነበረ ትዝ አይለኝም። ዋዛ እና ቀልድ የሚመስል ነገር ቢኖራትም፡ ጥሩ ስሜት የሚሰጥ ነገር ያላት የአስር-ሳንቲም መጽሐፍ ነበረች። ለእኔ ግን፡ የእግዚአብሄር የሚመስል ነገር፡አግኝቼባታለሁ። ከታሪኮቹ መካከል አንዱ እንዲህ ይጀምራል። አንድ ቀን ማለዳ በትልቅ የዶሮ እርባታ ውስጥ፣ መታወቅ ያለበት እውቀት ሁሉ አለኝ ብሎ የሚያሰብ አንድ ትንሽ አውራ ዶሮ ነበረ። ወደ እንዲት ካርቶን በርሮ ወጣና፣ ካርቶኑን አምስት ወይም ስድስት ጊዜ ያህል በእሩ መትቶ፣ ትንሿ ጭንቅላቱ ወደ ኋላ በማድረግ አውራ ዶሮ ሲጮኽ ሰምታችሁ የማታውቁት ጩኸት ጮኸ። እና የሌሎቹ፡ አትኩሮት ሳበ፣ እና እንዲህ አላቸው፡- “በዚህ በደሮ ሰፈራ ኗሪዎች የሆናችሁ ክቡራት እና ክቡራን፣ ዛሬ በዚህ ማለዳ በቅርብ ስላረቀቅነው ታላቁ ሰርዓተ ትምህርት በተመለከተ ለሁላችሁ መናገር ፈልጌአለሁ።” መነጽሩን እሩ ስር ጎተት እያደረገ፡- “በጥናቱ ላይ እጅግ ብዙ እውቀት አግኝቼበታለሁ፣” አላቸው። አክሎም፡- “እኛ ዶሮዎች ተጨማሪ እውቀት በመጠቀም እራሳችንን ማሻሻል እንችላለን አላቸው። ስለዚህ፡ እንዲህ በሚባል ሰፈር ወይም ጉድጓድ አካባቢ ከቆፈርን፣ እኔ ልንገራችሁ፣ አብልጠን እንድንጮኽና፣ ውብ ላባዎች እንዲኖረን የሚያስችል ልዩ ቪታሚን እናገኛለን። ሌላም፡ ኦህ፡ እራሳችንን-ማሻሻል እንዴት እንዴት እንደምንችል እነግራቿለሁ አላቸው።።”

21 እና ትንንሾቹ ቄቦች ትናንሽ ቀይ ማበጠሪያዎቻቸው ጋር፣ እየተሳሳቁ “እሱ ግን ፍቅር ነገር ነው አይደል?” አሉ፤ በርግጥም አደናነቁት። “ኦህ፡ የተለየ አውራ ዶሮ ነው አሉት!” እነዚህ አንዳንዶች የሰሚናሪ ሰባኪዎችን ያስታውሰኛል። “እጅግ ብሩህ ሰው ነው! ከሌሎቹ ዶሮዎች ጋራ ምን ጊዜ ማጥፋት ያሰፈልጋል፡ ሁላችንም እንድንከተለው ይገባል አሉ።”

22 ከዚያ በኋላ፡ ተናጋሪው ንግግሩ ከመጨረሱ በፊት፣ እምብዛም የማይሰቡ ላባዎች የነበሩት አንድ ዶሮ ከመካከላቸው ወጣና፡ ከዶሮዎች ግቢ ከሌሎች ዶሮዎች መሀል እየሮጠ መጥቶ፣ እንዲህ አላቸው፡- “ሰዎች፡ አንድ ደቂቃ ቆዩ! ሬድዮ ላይ ሰበር ዜና ሰምቻለሁ። የዶሮዎች ዋጋ በፓውንድ አራት ሳንቲም ጨምሯል፡ ነገ ሁላችንም እንታረዳለን! እውቀታችሁ ምን ሊጠቅማችሁ ነው አለ?”

23 ወንድሜ ሆይ፡ ይህ ሁሉ የምናጠራቅመው እውቀት፡ ምን ሊጠቅመን ነው? እኛ'ኮ ስድስት ጫማ አፈር ነን! ሁላችንም በየኢንቹ እና በየደቂቃው እንሞታለን። እውቀታችን ከንቱ ነው። እሱን ማወቅ አለብን። እነሱ ግን ይሄን ያደርጋሉ።

24 ከዚህ በፊት አንድ ካናሪ ስለሚሉት ወፍ የተናገርኩት ነገር ነበረ፣ እና መታወቅ ያለበት እውቀት ሁሉ—ያወቀ መስለውና፣ እና ሌሎች ካናሪዎች ስለ ሰዎች ልጆች ብዙ መናገር እስኪችል ድረስ እውቀት አወቀ። ወደ ጎጆው በርሮ ወጣና፡ የሰው ልጆችን ምን ያህል እንደሚያውቃቸው መናገሩን ጀመረ። እና፡ አንድ ፕሮፌሰር ከፐርዱ በድንገት መጥቶ፡ እጅግ-የመጠቁ ቃላት ይናገረው ጀመር፣ ይህ ታናሽ ሰው ግን አይኖቹን እያቁለጨለጨ ራሱን ዞር አደረገና… መቼም፡ አይኖች አሉት፡ ፕሮፌሰሩን ማየት ችሏል። ጆሮዎች አሉት፡ ሰምቶታል። ነገር ግን፡ በርግጠኝነት፡ ስለሚለው ነገር አላወቀም። ለምን? አእምሮው የካናሪ ስለሆነ። የወፍ-ራስ ብቻ ስለሆነ ነው። ያለችው ይህች ናት። የሰው አእምሮ ስለሌለው፡ እንደ ሰው ማሰብ አይችልም።

25 ሰውም ቢሆን እንደ እግዚአብሄር ማሰብ አይችልም! ሰዎች ናችሁና፡ በዓለም ያለው እውቀት ሁሉ ከካናሪ ራስ የሚያልፍ አይደለም። በምትሰሩት ሁሉ፡ እራሳችሁን መጉዳት ብቻ ነው። የክርስቶስ ልብ ይኑራችሁ።

26 ሰዎች እየሄዱ ድርጅቶችን የሚቀላቀሉበት፡ እና ዳግም ከመወለድ ይልቅ በእጅ በመጨባበጥ የሚተኩበት ምክንያት፣ አዲስ ልደትን ገሸሽ ለማለት ነው። አዲሱን ልደት አይፈልጉትም። በተጨማሪም እነሱ—ይህ ነገር በመጽሀፍ ቅዱስ እንደምናስተምር ያውቃሉ፡ ስለዚህ በሌላ ነገር ሊተኩት ይፈጋሉ። ጴንጤቆስጤዎች እማ የባሰባቸው፡ ለየት አርገው መተካት ይሞክራሉ! ዘመናዊ እንዲሆን ይፈልጉታል። ዘመናዊ መሆን አለበት፦ "እጅ ተጨባብጠን፣ ተረጭተን፣ ወይ ደግሞ ተጠምቀን ወዘተ፡" የቤተክርስትያን አባል እንሆናለን። አዲስ ልደትን ይፈሩታል። አንዳንዴ የብራንሃም ተበርናክል እራሱ እየፈራች እንዳለች አምናለሁ!

27 አሁን፡ ሁላችንም እንደምናውቀው፡ ልደት መመሰቃቀል ያለበት ቢሆንም፡ ምንም ቢሆን፡ ወይም የት፡ አይገደኝም። ልጅ ገለባ ላይ ይወለድ፣ ደረቅ ምድር ቤት ላይ፣ ወይም በፒንክ-ባጌጠ ሆስፒታል ውስጥ፡ ምንም ይሁን፡ ሁሉም መመሰቃቀል ነው። የጥጃ አወላለድ፣ ወይም የምንም ነገር አወላለድ ሁሉ፡ ምሰቅልቅል ነው።

28 አዲሱ ልደትም ከምሰቅልቅል የዘለለ ሌላ ነገር የለውም! ሰዎች ግን አይሞቃቸው አይበርዳቸው፦ "እጅ ወደሚጨባበጡ ጋር መሄድ ይሻለናል። ጩኸት እና ሁከት፣ መሰውያው ላይ መማታት እና ማልቀስ ወደሌለበት መሄድ ይሻለናል።" እጅጉን ሰው መሆን ትፈልጋላችሁ! እኛን የሚያስፈልገን፡ ጨርሶ መሞት፣ ህይወት የሚገኝበት ነገር፣ ልደት ነው!

29 ዘር'ኮ፡ እንዲት ድንች፣ የድንች ዘር ወስዳችሁ፣ መሬት ላይ ቅበሯት። አዳዲስ ድንቾች እስክታፍሱ ድረስ፡ የመጀመርያዋ ድንች መበስበስ አለባት። ቦቆሎ ሳይበሰብስ አዲስ ህይወት አይሰጥም።

30 እንዲሁም ደግሞ ወንድም ይሁን ሴት እውቀታቸው ይሁን የግል ሰብዕናቸው ካልበሰበሰ፡ ካልሞተ፡ በምሰቅልቅል፡ እና በለቅሶ፡ በመሰውያው ስር ካልሞተ፣ ግድ የሌላቸው ሁሉ መጠምጠሚያችሁን ጥላችሁ፣ በጌታ

መንፈስ ዳግም ካልተወለዳችሁ አዲስ ልደት በፍጹም የለም። ኡኡ ብትሉ፣ በልሳን ብትናገሩ፣ ወደላይ-እና-ወደታች ብትዘሉ፣ ራሷ እንደተቆረጠች ዶሮ ብትፈርጡ አልጨነቅም፣ ምክንያቱ አዲስ ህይወት እያፈራችሁ ናችሁ! ነገር ግን በሌላ ነገር እንተካዋለን፡ አዎን፡ ዘመናዊ ነገር እንፈልጋለን።

31 በቀደም፡ አርብ 'ለታ፡ እኔ እና ሚስቴ ገበያ ሄደን ነበር። እዚህ ላይ ለመደጋገም ፈልጌ አይደለም። ብቻ ጎዳናው ላይ እየሄድን ሳለ፡ ራሴን ወዲህ እና ወዲያ ደጋግሜ ሳዞር፡ ራቁታም ሴቶች ብቻ። አይነ ሰውር ሆኜ በነበርኩ ጊዜ፡ እግዚአብሄር አይኖቼን ከፈወሰ፡ ትክክል የሆኑ ነገሮች ብቻ እያለሁ ብየ ቃል ገብቻለሁ። እና መኪናየ ውስጥ መሰቀል እንጠልጥያለሁ። እንዲህ ዓይነት ነገሮች ሳይ፡ መሰቀሉን እየት አደርግና፡ መሰቀሉን እያየሁ፦ "አምላክ ሆይ፡ ይሄ'ኮ ለኔ መጠጊያየ ነው፡" እላለሁ።

32 ሴቶቹን አየኋቸው። ሜዳም እንዲህ አለች፦ "ዛሬ'ኮ ቀሚስ ያደረገች አንዲት ሴት እንኳ አላየንም።" "ቢል፡ በሰውነቷ ላይ ትንንሽ ማንገቻዎች ያደረገችውን ያቺን ሴት ተመልከታት፡" አለችኝ፡ "አሁን ይቺ ሴት ይህ ስህተት መሆኑን አታውቅም ነው የምትለኝ? " አለችኝ፡ "ባታውቀውም ስሕተት ነው፡ ስለዚህ ከትክክለኛ አስተሳሰብ ወጪ ናት፡" አለችኝ።

33 "እንዴ ቆዪ፡ ማር። እሷ አሜሪካዊ ስለሆነች፣ አሜሪካውያን እንደሚያደርጉት ታደርጋለች፡" አልኳት። "ውዴ፡ የሆነ ጊዜ ፊንላንድ ውስጥ ነበርኩ፡" አልኳት።

34 እኔን የተቀበለኝ ዶክተር ማኒነን የተባለ አንድ ሰው፡ ጠየቅኩት። "ሳውና፡" የሚሉት የጤና—እጥበት ጋር እየሄድን ነበር፡ ያስገቧችሁና ትኩስ ውሃ ይደፋበታል፣ ወይም ትኩስ ድንጋይ ላይ ውሃ ይደፋሉ፡ ከዚያ ያልብሻል። ከዚያ በኋላ በበረዶ ውሃ ላይ ያዘልሉሻል፣ ከዚያ ትወጫለሽ። ከዚያ በኋላ ወደ አንድ ክፍል ይወስዱሻል፣ በዚያም ደግሞ ነርሶች አሉ፣ ወንዶችን የሚያሹ ሴቶች ናቸው (እንደውም እራቁታቸው ናቸው)፣ ከዚያ በኋላ ወደ ገንዳው ይመልሷቸዋል። እኔ ብሆን አልገባም። "ይሄ'ማ ስሕተት ነው ዶክተር ማኒነን፡" አልኩት።

35 እሱም አለ፦ "እሺ መልካም፡ ሬቨርንድ ብራንሃም፡ ስሕተት ይሁን። ታድያ የእናንተ አሜሪካ ዶክተሮችስ ሴቶቹን እራቁታቸውን ገልጠው ጠረጴዛ ላይ አስተኝተው፣ የሰውነት ክፍላቸውን—የሰውነት ክፍላቸው ሁሉ የሚመረምሩስ? በሆስፒታል ውስጥ ያሉ ነርሶቻችሁስ"?

36 "ይቅርታ አርግልኝ ማኒነን፡ ወንድም ማኒነን፣ አንተ ትክክል ነህ፡" አልኩት።

37 ምንድነው? ልማድ ነው። በፓሪስ ሳለሁ የወንድ እና የሴት መጸዳጃ ቤት አንድ ነው፡ እና ማመን አልቻልኩም። የሴት እና የወንድ መጸዳጃ ቤት ሁለቱ መንገድ ዳር ላይ መሆኑ፡ ሊገባኝ አልቻለም። ወንድ ከሴት ፍቅረኛው ጋር፣ እና ሴቶች ዋና ለመዋኘት ወደ ባህር ዳርቻ ሲሄዱ ማመን አልቻልኩም፣ ልብስ የሚቀይሩበት ክፍል የላቸውም፡ እስከ መጨረሻዋ ልብስ ድረስ እንዲሁ ያወልቁታል፣ ጀርባቸውን ዞር ያደርጉና ስስ ማንገቻ አጥልቀው ወደ ዋና ይገባሉ፣ ግን እንደዚያ ነው። የፈረንሳይ ልማድ ነው። ማንም አትኩሮት አያደርግባቸውም።

38 አፍሪካ ውስጥ፡ ሴት እና ወንድ፣ ወጣት እና አዛውንት፣ አንዳች ልብስ ሳይለብሱ፡ ማሳው ላይ ይሄዳሉ። መጸዳጃ ቤት፡ ወይም ሌላ፡ ምን እንደሆነም አያውቁትም፣ ወይም ደግሞ እንዳይተያዩ ተደባብቀው አያውቁም። ልዩነቱ ግን አያውቁትም። ልዩነቱን አያውቁም። በየአገሩ ግን ልማድ ነው።

39 እኛ ግን፦ "የኔ ማር፡ እኛ እንለያለን፡ የሌላ አገር ዜጎች ነን። ስደተኞች እና መጻተኞች ነን፡ እነኚህ ነገሮች ስሕተት የሚሆኑብንም ስለዚህ ነው። መጽሐፍም ሲናገር፦ 'ከሩቅ ሆነው፡ ተሳለሙት፡ እንግዶች እና መጻተኞች እንዲሆኑ ታመኑ፣ የምትመጣውን ከተማ ይጠብቃሉና።'"

40 በጣልያን፣ በፈረንሳይ፣ በአፍሪካ ውስጥ ወንድ ይሁን ሴት፣ በመንፈስ ቅዱስ ዳግም የተወለደ፡ በየትኛውም አገር ሆኖ፡ እነዚህን ነገሮች አያደርግም። እነዚያን ዓይነት ልብሶች አይለብሱም። እነዚያን አይነት ድርጊቶች አይፈጽሙም፡ ምክንያቱ እግዚአብሄር የሚመራት እና የሰራት የሌላ አገር ዜጎች ናቸውና። እኛ ከሰማይ ነን። በውስጣችሁ ያለው ያ መንፈስ፡ እርሱ ያንቀሳቅሳችኋል። አሜሪካዊ ከሆናችሁ፡ አሜሪካውያን የሚያደርጉትን ታደርጋላችሁ። ፈረንሳዊ ከሆናችሁ፡ ፈረንሳውያን የሚያደርጎትን ታደርጋላችሁ፡ ሌሎችንን ትነቅፋላችሁ። የእግዚአብሄር ከሆናችሁ ግን፡ በሰማያት የሚደረገውን ታደርጋላችሁ፡ መንፈሳችሁ ከላይ የመጣ ነውና እሱን ይቆጣጠራችኋል።

41 ልትገነዘቡት የሚገባችሁ ትንሽ ነገር አለ። በቅዱስ ቃል ውስጥ፡ አዲስቷን ከተማ የሚጠባበቁ ሰዎች፡ ድርጊታቸው ይለያል። ሰደተኞች እና መጻተኞች መሆናቸውን ታምነዋል። የቃየን ወገን ግን፡ ቅብዝብዝ እና ነውጠኞች ሆኑ። ክርስትያኖች ግን መጻተኞች እና ሰደተኞች ናቸው። ተቅበዝባዥ ቤት የለውም፣ ነውጠኛ ደግሞ ክፉ ሰው ነው። መጻተኛ ግን፡ ወደ ቤቱ የሚመለስበትን መንገድ ፍለጋ፡ ከሌላ እውነተኛ ምድር የሚመጣ እውነተኛ ሰው፣ አንዳች ነገር እንዳለው የሌላ አገር ዜጋ መሆኑ ይታመናል። ይሄው ምክንያቱ ይህ ነው።

42 ነገር ግን እነዚህን ነገሮች የሚያደርጉ ሰዎች፡ እነዚህን አልባሳት የሚለብሱ ሰዎች፣ አንድ ነገር ልንገራችሁ። በደቡብ አፍሪካ፡ ሰላሳ ሺህ እራቁታቸው፣ ጥሬ አህዛብ፣ ባህላዊ የአገሩ ተወላጆች አይቻለሁ። አሰራ ሰድስት-፡ አሰራሰምንት-፡ የሀያ-ዓመት-ሴቶች፣ ብጣሽ ልብስ ያልለበሱ ወንዶች፣ ፊታቸው ላይ ጭቃ ተቀባብቶ፡ ተቀልሞ፣ አፍንጫቸው ላይ አጥንት፡ ጆሮአቸው ላይ የእንጨት ክምር እንጠልጥለው፡ የሰው ይሁን ሌላ አጥንት ጸጉራቸው ላይ፣ የእንሰሶች ጥርስ በሰውነታቸው ላይ አንጠልጥለው፡ ወደ ዓለም እንደመጡባት ቀን እራቁታቸው ነበሩ፡ ደግሞም አያውቁትም። በፊታቸው እየወደቁ መንፈስ ቅዱስ እየተሞሉ፡ ክርስቶስን በተቀበሉት ጊዜ ግን፣ ተነስተው የሚለበስ አግኝተው ለመልበስ ሲሄዱ ግን፣ በእፍረት እጆቻቸውን ደረታቸውን አቅፈው ይሄዱ ነበር። ለምን? ለዚህች ዓለም መጻተኞች እና እንግዶች ስለሆኑ። ሃሌሉያ! አዎን፡ ጌታየ። ከሱ ርቀው ነበርና።

43 ኦህ፡ አዎን እነዚህ ሰዎች፡ እራሳቸውን ክርስትያን ብለው ይጠራሉ። የቸርቾች አባላት ናቸው። ይሄዱና እንዲህ ይላሉ፦ "እኛ ሜቶዲሰቶች ነን። ባፕቲሰቶች ነን። ጴንጤዎች ነን። እኛ ሰባተኛው-ቀን አድቬንቲሰቶች ነን። እና **እንዲህ፡ እንዲያ**፡ እና **ሌላ** ነን ይላሉ።" ይሄኛው ከዚህ

ጋር በምንም አይገናኝም። መንፈሳችሁ፡ በውስጣችሁ የሚገኘው ህይወት፡ ያነቃቃችኋል ማንነታችሁን ይነግራችኋል። "በፍሬአቸው ታውቁአቸዋላችሁ፡" ብሏል ኢየሱስ።

44 ቤተክርትያን እስራኤል በመጀመርያ እንደሆነች፡ ሆናለች። እግዚአብሄር ራሱ ንጉሳቸው ነበር። የአሕዛብ ወገኖች ግን ነገስታት እንዳላቸው አዩ። አሕዛብ ሁሉ ነገስታት እንዳላቸው አይተው፡ እንደ አሕዛብ መንግስታት ስራ ማድረግ አማራቸው፣ ለራሳቸውም ንጉስን አቆሙ። ይሄን ባደረጉ ጊዜም፡ ችግር ላይ ወደቁ። ከዚያ ቀስ በቀስ መግባት ጀመረ። ቀስ በቀስ ዓለም በውስጣቸው መስረጽ ጀመረች። በመጨረሻም በአክዓብ እጅ ወደቁ። አንድ ንጉስ በመጠኑ እሱን እየመሰለ ይመጣል፡ በመጠኑ እሱን የሚመስል፡ በስተመጨረሻ ግን ህይወታቸውን ጨፍልቆ ወሰደባቸው። እነሱም ቀጠሉ። እውነተኛው ንጉስ በመጣ ጊዜ ግን፡ አላወቁትም።

45 ቤተክርስትያን የፈጸመችውም ይሄው ነው። ይሄውላችሁ። ማደጎ ነው። የማደጎ ፖለቲካ፣ እና ትምህርት ነው። የማደጎ ድርጅቶች፣ ማሕበረሰብ፣ ትልልቅ ቸርቾች፣ እጅግ ተናጋሪ ሰባኪዎች ናቸው። ትክክለኛው ንጉስ በመጣ ጊዜም፡ አላወቁትም፡ ንጉሳቸው የሆነውን እራሱን መንፈስ ቅዱስን ሰቀሉት። ሳቁበት እና ተሳለቁበት እንጂ፡ አላወቁትም። አይሁዶች በመሲሐቸው ያደረጉት፡ ቤተክርስትያንም መሲሕዋ ላይ ያንኑ አደረገች። አያውቁትም። መንፈሳዊ እይታ የላቸውም፣ ምክንያቱም በሚያዩዋቸው፣ ታላላቅ ሕንፃዎች፣ ከዓለም ጋር ለማወዳደር እየሞከሩ በዓይኖቻቸው በጣም-የተሰነዱ ናቸው። እራሳችንን ከዓለም ጋር ለማወዳደር አልተመከርንም—አንመክርም። የተመከርነው እራሳችንን ዝቅ ለማድረግ ነው።

46 እና፡ በእግዚአብሄር ፊት፡ አንዱ እንደ ብዙ ህዝብ ነው። እና ዛሬ ዛሬ በወንጌላውያን የፈውስ ጉባኤዎች ዘንድ፡ ብዙ ውድድር፡ ብዙ ተወዳዳሪዎች አሉ። አንደኛው፡- "በጣም ጥሩ፡ ጌታ ይባረክ፡ ብዙ ሺህ አለኝ። ከአንተ ጉባኤ ይልቅ የሚበልጥ ጉባኤ አለኝ" ይላል። ምን ልዩነት ይፈጥራል? አንድም ይኑረን አንድ ሚልየን፡ ምን ልዩነት አለው? ለጌታ ታማኝ ነን ወይ? ለቃሉስ እንታመናለን ወይ? የመንፈስ ቅዱስ ፈተናስ በጽናት እናልፈዋለን? እውነት ነው ወይ? ነው ዋናው ነገሩ።

47 መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ግን እናመቻምቻለን። ብዙዎች የጴንጤቆስጤ ሰዎች፡ መሰረታዊ በሆኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች ላይ፡ ያመቻምቻሉ። እነዚህ… እንደው እኔ ሰሜት መጉዳት አልፈልግም እንጂ። ወንጌል ሰባኪ ስለሆንኩ ግን፡ በራሴ ቤተ ክርስትያን ውስጥ ሆኜ፡ በቤተ ክርስትያኔ፡ እነዚህን ማሳወቅ እንዳለብኝ—ይሰማኛል። መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዲህ አይነት ነገር እንደሌለ የሚያውቁ አስር ሺህ የሚያህሉ የጴንጤቆስጤ ሰባኪዎች ግን አሉ "በአባት፣ በልጅ፣ በመንፈስ ቅዱስ" ስም የሚባል ጥምቀት እንደሌለ፡ ኮ ያውቃሉ። ሊቀ ጳጳሱም ይሁን፣ ማንኛውንም ሰው ይቅረብ፣ "በአባት፣ በልጅ፣ በመንፈስ ቅዱስ" ስም የተጠመቀ አንድ ሰው ካለ ያሳየኝ። እነሱ ግን ተቋሞቻቸው ይሄን ስለሚያደርጉ ብቻ፡ ያመቻምቻሉ። በታሪክ ውስጥ፡ በአዲስ ኪዳን፡ በመጀመርያዎቹ ሶስት መቶ አመታት አንድም ሰው አታገኙም፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ከተጠመቁ በቀር አንዳች አታገኙም። ምንድነው? ተቋም ነው። ይሄን ያደረገው። አመቻማቾች!

48 ዛሬ ሁሉንም የጎዳና ሰባኪዎችን’ማ ከመንገድ ላይ አስወግደውአቸዋል። ከበሮውን ከቤተ ክርስቲያን አውጥተዋል። ክብሩን ሁሉ ከቤተ ክርስቲያን አውጥተው፣ የሴሚናሪ ስብከት፣ ትንሽ የአውራ-ዶሮ ማበጠሪያ ስብከት ይዘዋል፣ በማኅብረሰብ ውስጥ ሁሉም የተከበሩ ናቸው፣ የሴቶቻቸው ሰውነት በአጫጭር ጠባብ ልብሶችን ውስጥ ተጠቅጥቋል፣ ወንዶቻቸው ሲጋራን እያጨሱ፣ ክፉ ቀልዶች እየቀለዱ የሚቆምሩ ናቸው። በእግዚአብሄር ፊት ነውር ነው! እንደሚሰቀጥጥ አውቃለሁ፡ ነገር ግን አንድ ሰው አንዳች ነገር ማለት ያለበት ወቅት አሁን ነው። ማመቻመች፣ ማሳጣት፣ ዓለምን መምሰል!

49 ከእግዚአብሔር በቀር ማንም ከጎኔ ባይኖር፡ ብቻየን ብጸና እንኳን ግድ የለኝም፣ የእግዚአብሄርን መጽሐፍ ቅዱስ እውነት እሰብካለሁ ለእሱም እጸናለሁ። ብሞትም’ኳ፡ ስለ እውነት እጸናለሁ። በትክክል። እውነት ያስፈልገናል። እንደ እግዚአብሔር ቃል እመዝናለሁ እንጂ፡ እንደ ቤተ ክርስቲያን አልመዝንም።

50 ደሊላ ግን፡ አስተውላችኋል? ሳምሶን ሐይል እንዳለው ታውቃለች። ሐይሉ ያረፈበት ስፍራ ግን አታውቅም። ሳምሶን የተሞላው አንዳች ሐይል መኖሩ እንጂ፡ ሐይሉ ይሄ ነው ማለት አልተቻላትም፡ ስለዚህ ማወቅ ፈለገች። ስለዚህ፡ እንደ ደሊላነቷ፡ ሳምሶንን በውበቷ ማባበል ተያያዘችበት። አቤት፡ አለባበሷ ልዩ ነው። እንደ ዘመኑ ልጃ-ገረዶች በፊቱ ቀጭ-ቋ እያለች፣ እና—እና ሌላ እያደረገች ትራመዳለች፣ ሌላ ነገር እንደሆነች አክት ታደርጋለች፡ ሳምሶንን ለማጥመድ፡ እርቃኗን ተውረገረገች።

51 ዓለም ቤተክርስትያንን የሰራቻት ድርጊት ይሄው ነው። አሁን ታላቁ ሐይልህ የት ነው?

52 “አዎን፡ ከተደራጀን፡ ኃይሉ ይሰብራል።” የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ፈጽማዋለች።

53 “ሳምሶን ሆይ፡ ፍልስጥኤማውያን መጡብህ።” ከዚያ በኋላ ሉተር ብቅ አለ።

54 ከዚያ እንደገና ተደራጁ። “በሌላ ገመድ ብታስሩኝ፡ እሸነፋለሁ አላቸው።” ያላቸውን አደረጉ።

55 “ሳምሶን ሆይ፡ ፍልስጥኤማውያን መጡብህ።” ምን ተፈጠረ? ዌስሊ ብቅ አለና ገመዶቹን በጣጠሰ።

56 “ሳምሶን፡ እኔ እንደምወድህ አታውቅም? እስከ አሁን ድረስ አታልለኸኛል። በል አሁን፡ በልብህ ውስጥ ያለውን እውነት አጫውተኝ።”

“ይሁን እሺ፡ በሌላ ገመድ እሰሩኝ።”

57 “እሺ ይሁን፡ አሁን ይሄን እናደርጋለን።” ምንድነው እሱ? የሃይማኖት ተቋም ገመድ ነው።

58 “ወደ የትኛውም የሃይማኖት ተቋም እንዳልሄድ፡ ነጻ አድርጉኝ። ከዚያ፡ ልንገራችሁ፡ ትሰባብሩኛላችሁ።” ከዚያ ጴንጤቆስጤዎች ተነሱ። ኃይልህ ወዴት ነው?

“ፍልስጥኤማውያን መጡብህ።” እናም ገመዶቹን እንደገና በጣጠሰው።

59 ከዚያስ ምን ሆነ? ለፓስተሮቻቸው ትላልቅ የስነ መለኮት ዶክትሬት ያላቸው፡ ጴንጤቆስጤዎችን፣ ኃያላን ሰዎች አገኘ። ሜቶዲስቶች ወይም ባፕቲስቶች፣ ወይም ሌሎቻቸው ያላቸውን ያህል፣ ትምህርት እና ሥርዓት አላቸው። ወደ ቤተክርስትያን ስትገቡ “አሜን” እንኳን አትሰሙም፡ በሰሜናዊ ክበብ እንዳሉ ስኪሞስ ዓይነት የቀዘቀዙ ናቸው። ቀዝቃዛ! ግዴለሽ! “ሳምሶን ሆይ፡ አሁንም ፍልስጥኤማውያን መጡብህ።”

60 ፍልስጤማውያን መጡብሽ፡ አሜሪካ። የመንፈስ አንድነት የት አለ? የጴንጤቆስጤ አንድነት የት አለ? አሰምብሊስ ኦፍ ጋድ፣ የተባበሩት፣ እና ቸርች ኦፍ ጋድ፣ እና **ይህ፣** እና **ያ፣ ሌላኛው፣** እያንዳንዳቸው የተለያዩ ኢዝሞች አሏቸው፣ ይሄኛው **ከዚህ** ጋራ፡ ያኛውም **ከዚያ** ጋር ነው። አንድ ቤተክርስቲያን እስፖንሰር ካደረገች፣ ሪቫይቫልን ለማድረግ ወደ አንዲት ከተማ እስክንሄድ ድረስ በጣም ተለያይተናል፣ ሌሎቻቸው ፈጽመው አይካፈሉም። አሜሪካ ሆይ፡ ኮሚኒስቶች በአንቺ ላይ ናቸው።

61 ኃይላችን የት አለ? ክብራችን የት አለ? ምንድን ነው? ምክንያቱም ከእግዚአብሔር ኃይል ይልቅ የሰውን ጥበብ ተከተትለናል! ለምን፣ ሰባኪዎቻችንን በጣም ጠንካራ እና ግትር ሆነው አግኝቷቸዋልና፣ ሰዎች... እስኪያደራጁን፡ አንገተ ደንዳኖች እና ግትር እስክንሆን ድረስ፣ እንደ ድሮ በቤተክርስትያን ውስጥ የሚያለቅስ ሰምታችሁ ታውቃላችሁ? ማንም ሲያለቅስ አልሰማችሁም። የእንባ ጸላዮች ሰፍራ ከህንጻው ስር ደብቀውታል። ክብር ከቤተ ክርስትያን ርቋል። የተቻለንን ያህል ግትር በመሆን ከኋላ ቁጭ እንላለን። ነጻ አይደለንም። ታሰረናል። ዲያቢሎስ፡ በዘመናዊ አጋንንቶቹ፡ የሕያው የእግዚአብሔርን ቤተክርስቲያን አሰሯል። ትክክል ነው። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከእንግዲህ ኃይል የለም። ከእንግዲህ ነፃነት የለም። ህዝቡ በጣም ግትር እና ደንዳና ናቸው! እንዴት፡ እግዚአብሔር በጴንጤቆስጤ ሰዎች መካከል ቢመጣ፣ እግዚአብሄርነቱ እያሳያቸው፣ የትንሳኤው ኃይል በምልክቶች እያጸናላቸው እንኳ፣ አይነካቸውም። ክብር! ለምን፣ ውርደት ነው! እግዚአብሔር እየሠራ፣ ምልክቶችን እያደረገ፣ በመላ አገሪቱ ተጉዣለሁ፦ ሰዎች ተቀምጠው፣ አዎን፡ “ይህ ነገር፡ መልካም ይመስለኛል። ኦህ፡ እኔ አውቃለሁ እንዲህ ይደረጋል።” ምንም አይነካቸውም! ለምን? በደሊላ፡ በዓለም የታሰሩ ስለሆኑ። ሰንሰለት ውስጥ ናቸው።

62 አሁንማ ወደ ውስጣቸው ገብተዋል፣ ወደ ኮንፌዴሬሽን አሰሯቸው። “ሳምሶን ሆይ፡ ፍልስጥኤማውያን መጡብህ።” ምን ልታደርጋቸው ነው?

63 “ኦህ፣ እኛ ታላላቅ ቤተ እምነቶች አሉን።” አዎን። “ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ብዙ አባላት አሉን።” ታዲያ መንፈሱ የት አለ? መንፈስ ቅዱስ የት አለ?

64 ዲያብሎስ ያረገው ይሄ ነው። ቤተክርስትያንን አማለላት። ቤተ ክርስቲያን ማማለልን ቀጥሎበታል፣ “ወደ እኔ ኑ፡ ይህን እና **ይሄን** ካደረጋችሁ እዚሁ ታላቅ ድንኳን እሰጣችኋለሁ። ያንን አክራሪ ሰባኪአችሁ አባርሩትና፡ ሰሜት ያለው የስነ መለኮት ዶክተር የሆነ ሰው፡ ብትቀበሉ፣ ግዙፍ ግሩም እና የሚማርክ ቤተክርስትያን እንገነባለን ከዚያ በኋላ እንደሌሎቹ እንሆናለን።” ታሳፍራላችሁ!

ከዚህ ሁሉ ይልቅ አተር እና ቡና መለየት የማይችል፡ ነገር ግን በመንፈስ ቅዱስ የተሞላና፣ በእግዚአብሄር ሐይል፡ የማያመቻምቾች ይሻላችኋል።

65 ነገር ግን፡ አንዳንድ ቅዱስ ሰው፡ አይይ፡ ጉባኤውን አሸንፎ በልሳን ሲናገር፣ በጣም ግትር ናቸው፣ ወይም ትንሽ ቢጮህ፣ ወይም የሆነ ነገር ቢያደርግ፣ ሌሎቹ ዙርያውን በድንጋጤ ያዩታል። “ምንድነው? እሺ፡ ለምን ይላሉ? ከየት የወረደ ነው አክራሪ መሆን አለበት።” ይህ እውነት እንደሆነ እናንተም ታውቃላችሁ! አንድ ምስኪን ቅዱስ ሰው ገብቶ፡ ከደስታው የተነሳ፡ እጁን ከፍ አርጎ፡ እያነባ ጌታን ሲያመሰግን፣ አንድ ሰው በወንጌል ስብከት ምክንያት “አሜን” እያለ ሲጮህ፡ ሌሎቹ ምን እያለ እንዳለ ለማየት ዞር ይላሉ። ጴንጤዎች’ኮ ናቸው። ምንድን ነው ችግሩ? ሜቶዲስቶችን ዋቢ ስለምታደርጉ፣ ባፕቲስቶች ዋቢ ስለምታደርጉ፣ እነሱም ካቶሊክን ዋቢ ያደርጋሉ፣ ካቶሊክ ደግሞ ገሀነም ዋቢ ያደርጋል። እና፡ በአንድነት፣ ገሀነም ዋቢ ያደርጋሉ! ትክክል።

66 ደሊላ ወደ ታላላቅ ቸርቾች፡ የተመረጡ፡ የተማሩ አገልጋዮች፡ እና ወደ ከበርቴዎቹ አማልላችኋለች። “እየህ፡ ታውቃላችሁ፡ እዚህ **እገሌ-እና-እከሌ** ሚሊየነር ነው፣ እሱን ወደ ጉባኤያችን እንዲገባ ብናደርገው! ኦህ፡ ማይ!” ሚሊዮን ዶላሮች ቢኖረው ግድ የለኝም። ዳግመኛ ካልተወለደ፣ እሱ እዚያ መሆን አይገባውም። አርባ ካዲላኮች ቢኖሩት፡ ምንም ያለው ቢሆን፡ ዳግመኛ መወለድ አለበት፣ በቀጥታ ወደ አዲስ ልደት ደርሶ በመንፈስ ቅዱስ በመታደስ፣ በአዲስ ልደት ወደዚያ መምጣት አለበት፣ ንፍጡ እየወረደ (ይቅርታ አርጉልኝ)፡ እያ-ለቀሰ እና እየጮኸ፡ እንደሌሎቹ ሁሉ እየተመላለሰ፣ እንዳገኘውም ለማረጋገጥም በኑሮው ህይወት መኖር አለበት። አሜን። የሚያስፈልጋችሁ ይሄው ነው።

67 “ሳምሶን ሆይ፡ ፍልስጥኤማውያን መጡብህ።” ኮሚኒስቶች መጡብህ። ዓለም መጣችብህ። ዲያብሎስ መጣብህ።

68 ወደ ኋላ ተመልሰው የእግዚአብሔር መንፈስ ተአምራትን ሲያደርግ እና የትንሳኤውን ነገር ሲያደርግ፣ ኢየሱስ የገባውን ቃል ያዩና፡ እንዲህ ይላሉ፦ “ታውቃለህ፣ ወንድም ብራንሃም’ኮ አእምሮ የማንበብ ብቃት አለው። ፓስተራችን የዲያብሎስ ነው ብሏል።”

69 እናንተ ምስኪን፡ ግብዝ፡ ተላላ አክራሪ፡ ትንኝ አጥሪዎች፣ የበግ ለምድ ለበስ ተኩላዎች! ኢየሱስ እንዲህ ብሏል፦ “እኔንስ ብታውቁኝ፡ ቀኔን ባወቃችሁ ነበር።” እናንተን ግን እንደ ተቀረው ዓለም ለማድረግ የሚጥሩ ብዙ የሳኦል ክምሮች አሏችሁ።

70 በቃል ላይ የማያመቻምቹ የእግዚአብሄር ሰዎች ያስፈልጉናል፣ ስለ እውነት የሚሰብኩ በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ላይ የሚጸኑ።

71 ዓለም ግን ምን አደረገች? ኃይላችሁን ሁሉ ላጨች። ናዝሪን፣ ጴንጤቆስጤ ሆናችሁ ተወልዳችሁ ነበር፣ ዓለም ግን ሐይላችሁን ሁሉ በርግጥ ላጨች። አሁን እንደሌሎቹ ሁሉ ግትር ሆነናል።

72 ምን ልናደርግ ነው? ምንድነው የሚሆነው? ይሄን ስብከት ለማጠቃለል ሳስብ አንድ ታላቅ ነገር አለ።

73 ሳምሶን እንደታሰረ! መነቃቃት ሊኖር አይችልም። ታማኙ ወንድማችንን፡ ቢሊ ግራሃምን ሰሙት፣ “ሪቫይቫል በዘመናችን!” ኦራል ሮበርትስ የሚጮኸውን ሰሙት፣ “ሪቫይቫል በዘመናችን!” ሌሎቻቸውን ሰሟቸው፣ “ሪቫይቫል በዘመናችን!” ታሰረን ሳለን እንዴት ሪቫይቫል ሊኖረን ይችላል? መንፈስ ቅዱስን፡ በድርጅቶቻችን እና በባህላችን አሰረነዋል፡ የመንፈስ ቅዱስ ሪቫይቫል ሊኖረን አይችልም። አሜን። ከአየር ሁኔታው ጋር ተደምሮ፡ የሚለበልብ ሙቀት እንደሆነ አውቃለሁ፡ ነገር ግን እውነት ነው። በጣም ታሰራችሁ እና ግትር ሆናችሁ እንዴት የመንፈስ ቅዱስ መነቃቃት ሊኖረን ይችላል! “የአምልኮት መልክ፡” እንደሚኖራቸው መጽሐፍ ቅዱስ ተናግሯል። “የአምልኮት መልክ አላቸው፣ ኃይሉን ግን ይክዳሉ።” የማን ኃይል? የድርጅት ኃይል? የዓለም ኃይል? የቤተክርስትያን ኃይል ነው? የመንፈስ ቅዱስን ኃይል እንጂ! በቤተ ክርስትያን ውስጥ ሰውር እልፊኝ እሱ ነው። ቤተ ክርስቲያን የተማሩ ሰባኪዎችን፣ እና ትልልቅ ሕንፃዎችን እና የጌጥ ልብሶችን፣ ከጥንታዊው-ዓይነት መንፈስ ቅዱስ ይልቅ ስትቀበል፡ እረ ወደ ተልዕኮ ቢመለሱ ይሻላል። አሜን። እውነት። ሰዎች እየፈሩት እያሰሩት ደግሞም ካልተጠሙት፡ የመንፈስ ቅዱስ ሪቫይቫል እንዴት ይሆናል? ችግሩ እዚህ ላይ ነው።

74 “ፍልስጥኤማውያን መጡብህ።” ያለችንን አንዲት ተሰፋ፡ ሳምሶን በእስር ሳለ...

75 እሱን ሲይዙት መጀመሪያ ያደረጉት ነገር ምንድነው? መጀመሪያ፡ አሰሩት። ኃይሉን ወሰዱ፣ ምስጢሩን አገኙት። ምስጢራችሁን አግኝተዋል። ዓለም ምስጢራችሁን አግኝታዋለች። አሁን እናንተ ሴቶች እንደ ዓለም፡ ጸጉራችሁን ትቆራርጣላችሁ። ወንዶችም ሁላችሁ ዓለማዊ ድርጊቶች ትፈጽማላችሁ። ቀልዶችን እና ቆሻሻ ቀልዶችን መናገር፣ ችግር የለውም፣ ትንሽ ሲጋራ ማጨስ፣ ከጎሮቤት ሚስት ጋር መላፋት፣ እና የመሳሰሉ ነገሮች፣ ስራችሁን ላለማጣት ትንሽ መጠጣት። በሆዴ ብተኛ የሶዳ ብስኩቶችን እየበላሁ የቅርንጫፍ ውሃ ብጠጣ፣ በእግዚአብሔር ፊት ግን ንፁህ እና ያለ እድፈት ብሆን፣ በተገኘ ስራ ሁሉ ላይ ባላመቻምች ይሻለኛል። እውነት ነው። ትክክል። ለእግዚአብሄር ታማኝ ሁኑ።

76 “ሳምሶን፡ ፍልስጥኤማውያን መጡብህ።” የብራንሃም ተበርናክል ሆይ፡ ዓለማዊ-እሳቤ ሰርጎ እየገባብሽ ነው። እንዴት ነው ነገሩ? ምስጢራችሁን አሳልፋችሁ ሰጥታችኋል? ከጥቂት ዓመታት በፊት በአመድ ላይ በምትንከባለልበት ጊዜ እግዚአብሔር የሰጠህን ምስጢር አጋልጠሃል? በባህላዊ እና በልምዳዊ አምልኮ ምክንያት ሽልኮ እንዲወጣ ፈቅደሃልን? ምን ሆነሃል? እግዚአብሄር በጉባኤው መካከል ወርዶ ሲመላለስ እና ተአምር ሲያደርግ ሰዎችንም፡ የልብ ምስጢሮቻቸውን እና ያላቸውን ሁሉ ገልጦ እየተናገረ፣ የታመሙትን እና የተጎሳቆሉትን እየፈወሰ፣ ድንቆችን እና ምልክቶችን እያደረገ፡ በመንፈስ ቅዱስ ምክንያት፡ የተቻላቸውን ያህል ቃል እየተሰበካቸው፣ ሰዎች ግን፦ “ይሁን፡ መልካም ይመስለኛል። አንዳንዴ ካልተሰላቸን፡ ይሄን እያዳመጥን እንዝናናለን ይላሉ።” ብራንሃም ተበርናክልም። ፍልስጥኤማውያን መጡብህ።

77 ቃል በሚሰበክበት ወቅት፡ ያኔ፡ የጥንቱ አማኞች አይኖቻቸው እንባ አቅርሮ፣ ቃል ትንፍሽ ሳይሉ፡ እየተናነቃቸው፡ ሁለት ሶስት እርምጃዎችን፡ ወዲያ ወዲህ

እያሉ፡ በእግራቸው ተንቀሳቅሰው፣ ቃል ተመግበው! መንፈስ ቅዱስ በኃይል ተሞልተው! ቁጭ ሲሉ፣ “ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ቃል ሁሉ እንጂ በእንጀራ ብቻ አይኖርም።” ብራንሃም ተበርናክል፡ ፍልስጥኤማውያን መጡብሽ።

ጴንጤው፡ ፍልስጥኤማውያን መጡብህ።

78 አዎን በርግጥ፡ ያኔ ድሮ በድርጅታዊነት እጅግ በታሰራችሁ ጊዜ፡ በፍልስጥኤማውያን ተይዛችኋል፣ ፕሬስባይቴሪያን፣ የባፕቲስት፣ የሜቶዲስት፣ የካቶሊክ ወይም ሌላ ነገር ከመሆናችሁ የከፋ ምንም አይመጣም። ከሌሎቹ ጋር ምንም የሚያገናኝ ነገር የላችሁም።

79 ስለዚ፡ በኛ ጊዜ ሪቫይቫል? መደበኛው-የሪቫይቫል ሰጪው በዓለም ታስሮ ሳለ እንዴት ሊሆንልን ይችላል? እግዚአብሄር ዓለም ባለችበት አይመጣም፣ ልትመኩባት ብቻ ትችላላችሁ እንጂ። ከዓለም ጋር ካበራችሁ፡ ያኔ በቃ-ያበቃለታል። ዓለም እንድትገባባችሁ ስትፈቅዱ፡ እንደዓለም ለማድረግ ስትጀምሩ፡ ያኔ ያበቃላችኋል። ነገር ግን ከዓለም ሰንሰለቶች ሁሉ ተላቃችሁ፡ ወደ ጌታ ስትመለሱ፡ መልሳችሁ እስክትሄዱ ድረስ ጌታ ይጠቀምባችኋል።

80 ዛሬ ማለዳ መልዕክቴን ጠቅለል አድርጌ ለመጨረስ፡ የቀረልኝ ብቸኛ ተስፋ፡ ይህ ነው፣ “ሳምሶን ታስሮ ሳለ፣ አዲስ ፀጉር አቆጠቆጠ።”

81 ለእኛም እግዚአብሄር ዘመኑ ከማለቁ በፊት፡ የእግዚአብሄር መንፈስ ወርዶ የሚገባባት ሌላ ቤተ ክርስትያን ልኮልናል፣ በመንፈስ መገለጦች፡ ማርቆስ 16 የሚከተላት ቤተ ክርስትያን ናት፣ የሐዋርያት ስራ 2፡4፣ የሐዋርያት ስራ 2፡38፣ ሁሉ የሚከተላት ቤተ ክርስትያን ናት። ሐዋርያቶች ድንቆች እና ምልክቶች ይከተላቸው ነበር። ታላላቅ የትንሳኤው ምልክቶች ተከተላቸው። እኛ በእስር ሆነን፡ ጌታ ግን ለመጨረሻዋ ታላቅ እርድ፡ በሆነ ሰፍራ ላይ ሰብሉን እያሳደገ ይገኛል። ክርስትያን ወገኔ ሆይ፡ ይህ ዛሬ ለአንተ ያርግልህ፡ ማደግ የሚጀምረው ብርታት የአንተ ይሁንልህ። ይህ መልእክት በዛሬ ጠዋት፡ ይህ ወደሚሄድበት ምድር እንዲወጣ እጸልያለሁ፣ መልዕክቱ ለሰውነት ክፍላችሁ የሚጠቅመውን ቪታሚን ለማምጣት እንደሚረዳ አምነዋለሁ ይህም መንፈሳዊ ኃይል በውስጣችሁ እንደገና እንዲያድግ ያደርጋል።

አንገታችንን ደፍተን እንጸልይ።

82 ጌታ አምላክ ሆይ፡ የሰማይ እና የምድር ፈጣሪ፣ የዘለአለም ህይወት ደራሲ፡ የመልካም ነገር ሁሉ እና የመንፈሳዊ ሰጦታዎች ሰጪ ሆይ፣ ዛሬ ማለዳ እነኚህን ቃላት ወስደህ ልብ ላይ አኑርልንና፡ ጌታ ሆይ፡ አረጋጋቸው። ህዝቡም ጸሎቱን በዚህ ላይ ያድርጉ፡ ዓለም ቤተክርስትያንን በማማለል በስተመጨረሻም ኃይሏን እንዳገኘችው፣ ምስጢሯን እንደደረሰችበት፣ ምስጢሯ የተደበቀበት ማግኘቷና፡ በደንብ እንደላጨቻት ይወቁ። ድል ብለው የዘመሩትን፡ አንዴ ባለ ድል የነበሩትን ህዝብ ውስዳለች፡ ሁሉንም ላጭታቸዋለች፣ ዕሮብ ማታ ቴሌቪዥን ለማየት ቤት እንዲቆዩ አርጋቸዋለች። ደስታን ከልባቸው አርቃ፡ ለእግዚአብሄር ከሚኖራቸው ፍቅር ይልቅ ለዓለም ያላቸው ፍቅር አብዝታ ሰጥታቸዋለች። ሰለ ዓለማዊነት፡ ዓለምን አብዝታ ሰጠቻቸው፡ ወንጌልን በመሰበክ ከሚገኝ ደስታ ፈንታ ብዙ ዓለማዊ ሞኞትን። ብዙ እንቅስቃሴዎች እና ታላላቅ ባንዶች፣ እና ጩኸት እና እንቅስቃሴ ከሌለ፣ የደስታን እንባ ነፍስ

ውስጥ የሚያመጣውን፡መለኰታዊ ፈውስ የሚያመጣውን፡ የጥንቱን ወንጌል፡ ከእንግዲህ፣ ለቤተ ክርትያኒቱ የሐዋርያት ስጦታዎችን የሚመልሰውን፣ የዘመኑ መሲሕን፡ የተነሳው ክርስቶስን የሚመልሰላት አይፈልጉትም።

83 ነገር ግን እስራኤላውያን፡ ትክክለኛውን ንጉስ እንዳይከተሉ፡ በገዛ—ነገስታቶቻቸው ታሰረው እንደነበሩ፣ እውነተኛው ንጉሥም፡ በመጣ ጊዜ፡ አላወቁትም። ዛሬም እንዲሁ ነው። ጌታ ሆይ፡ የክብር ንጉስ በመንፈስ ቅዱስ መልክ መጥቷል፡ ግን፡ ጌታ ሆይ፡ አላወቁትም። አላወቁትም። ድርጅታዊነት ውስጥ ጠልቀው ስለገቡ፡ በድርጅታቸው ውስጥም ስለሌለ፡ ሊረዱት አይቻላቸውም። ጌታ ሆይ፡ ይህ ህዝቡ ዘንድ እንዲህ ያደረገው የዲያብሎስ ስራ ነው።

84 አምላካዊው ሳምሶን የሆኑትን፡ በልባቸው እውነተኞቹ፡ የሚያለቅሱ እና የሚያዝኑ፡ በጽናት እየለመኑ ያሉቱ፣ ጌታ ሆይ፡ አዲሱ ሰብል እስኪበቅል ድረስ፡ አብረው ይጽኑ፣ በጽዮን ዳግም ደስታ እስኪሆን፡ ይሄን ማወቅ የሚችሉ እና የሚረዱ መንጎች እስኪመጡ ድረስ፣ አሁን መረዳት የተሳናቸውን፡ መሲሑን እና ከዓለም የተሰወረውን ኃይል ማየት የሚችሉ ሰዎች እኪመጡ ድረስ የጸኑ ይሁኑ። ጌታ ሆይ፡ ይህን መረዳት ይችሉ ዘንድ፡ሰጠን። በኢየሱስ ስም ጸለይን። አሜን።

[በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ—ኤዲ.]
... አሁን ኃይል፣
ጌታ ሆይ፡ ኃይል ላክ አሁን
አጥምቀው ሁሉንም።

በላይኛው ሰገነት ነበሩ፣
ሁሉም በአንድ የተባበሩ
መንፈስ ቅዱሱ ሲወርድ
በጌታችን ተስፋ የተሰጠ።

ጌታ ሆይ፡ ኃይልህን ላክ አሁን፣
ጌታ ሆይ፡ ኃይልህን ላክ አሁን፣
ጌታ ሆይ፡ ኃይል ላክ አሁን፣
አጥምቀው ሁሉንም።

85 አቤት ሰወደው! በቃ ኃይሉን ላከላቸው! ሁሉም አንድ ሆነው፡ በላይኛው ሰገነት ነበሩ። ዓለም ከውስጣቸው ፈጽማ ወጥታለች። ባዶ ሆነው ነበር፣ መንፈስ ቅዱሰም ወረደባቸው።

86 ዛሬ የሚሉት፡- "ኑ፡ የቤተክርስትያን አባል ሁኑ፡ ሰሞቻችሁ በደብተር አስፍሩ። ወይም ሰግዳችሁ ይሏቸዋል፡- 'ክርስቶስ የእግዚአብሄር ልጅ እንደሆነ አምናለሁ፡' ብላችሁ ተነሱ።" ይሄ'ማ ዲያብሎሰም ያደርገዋል። አዎና። ይሁዳ በተጠመቀ ጊዜ ዲያቢሎስ ተጠመቀ። ይሁዳ ወጥቶ ወንጌልን በሰበከ ጊዜ ዲያብሎስ ወጥቶ ወንጌልን ሰበከ። ነገር ግን ዲያቢሎስ መንፈስ ቅዱስን አላገኘም። ይሀው ነው። ያንን ትንሳኤ፡ እዎን ብቻ የሚያውቅ፡ ያለ ቅንጣት ጥርጣሬ፡ ሰውር ኃይሉ የሚገኘው፡በዚያ ውስጥ ነው። አሜን።

87 በመሲሑ ላይ የነበረው፣ ያው መንፈሰ ቅዱስ፣ አሁንም በቤተ ክርሰቲያኑ ውስጥ ነው። ፈጽሞ አልሄደም። እዚሁ አለ። "ዘወትር ከእናንተ ጋር ነኝ፡ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ፡ በእናንተ ውስጥ ነኝ። አለሁ። እኔ የማደርገውን

ሥራ እናንተ ደግሞ ታደርጋላችሁ። እኔ ወደ አባቴ እሄዳለሁና ከዚህ በበለጠ ታደርጋላችሁ።"

88 ዓለም ግን ያመቻምችበታል፦ "አይይ፣ የእንደነዚህ ዘመን አልፈዋል!" እንድትሉ ነው ዲያብሎስ የሚፈልጋችሁ። እነሱ እንድታምሩ ይፈልጓቸዋል። እግዚአብሄር እንድትጠመቁ ይፈልጋል። እግዚአብሄር የሚፈልጋችሁ... እናንተ ግን፦ "አይይ፡ እኔ ይሄ ሁሉ አልወድም ገሊ-መሌ።" ሂድ እና ኑሮህን ኑር፡ ሂድ በሐጥያት ጸንተህ ኑር፡ በሐጥያትህ ኑር። ነገር ግን እስክትበሰብስ ነው፡ ለራስህ ሐሳቦችህ እስክትበሰብስ ድረስ፣ ለራስህ አካሄድ በሰብስህ፡ ዳግም እስክትወለድ ድረስ እና ዳግም ህይወት እስክትዘራ ድረስ፣ አዲሱ ህይወት ወደ ታች ከሚወርደው ይልቅ ሙሉ ለሙሉ የተለየ ይሆናል።

89 የበቆሎ ዘር ቢጫ ሆና ትወርዳለች፡ ስትነሳ ግን አረንጓዴ ናት። ደርቃ፡ ተጠቅልላ ትወርዳለች፡ ስትነሳ ግን ለስልሳ በንፋስ የምትወዛወዝ ሆና ትወጣለች። ኦህ፡ ክብር! ሀሌሉያ! ንፋስ መንፈስ ሲጀምር፡ ዘሯ ራሷን ከማንቀሳቀስ፡ ከመዞር በቀር አንዳች ነገር አታደርግም፣ ትንሽ—ትንሿ ብቅል በውዝዋዜ እና ደስታ፡ ታድጋለች፡ እራሷን ታበረታለች። በቆሎው በሰብሶ እስኪሞት ድረስ ግን ብቅሏ አትወጣም። መሞት ብቻ ሳይሆን፡ መበስበስ ጭምር። ተመልሳ አትመጣም፡ ነገር ግን ህይወት ከእሷ ይመጣል።

90 ከጥቂት ጊዜ በፊት እንዳልኩት፡ ልደት አስቃቂ ነገር ነው፣ ጭምልቅልቅ፣ ቁሸሸ፣ የመቆሸሸ ሁሉ መቆሸሸ ነው፣ ነገር ግን ሕይወት የሚገኝበት ነው። እራስህን ቆሻሻ ነኝ ብለህ ካሰብክ፡ የሜተዲስትነትህን ካሰብክ፣ ባፕቲስት እና ጴንጤቆስጤ መመርያዎች ቆሻሻ ካሰብክ፣ በመሰውያው ዘንድ ሙትና፡ አዲስ ህይወት ይመጣል። መንፈስ ቅዱስ ከዚያ በላይ እንድትሆን፡ እግዚአብሄርንም እንድታየው ያደርግሃል።

91 በተወደደች ቀን እናየዋለን። ሟች አእምሮ ከሚያሰበው በላይ በሆነች ቀን ላይ፡ እናየዋለን። ታምናላችሁ? ሟች አእምሮ ከሚያሰበው በላይ በሆነች ቀን ላይ፡ የነገ ደስታየ ይጠብቀኛል።

92 ትናንት ማታ እዚህ ጥግ ላይ ቆሜ ነበር፣ እና ትንሹ ረቢ ላውሰንን ያየሁት መሰለኝ። እዚህ በነበረ ጊዜ፡ ያረጀች ምርኩዙ ይልክና በአንገቱ እኔን ይጎትተኛል፣ አንገቴን በምርኩዙ ይዞኝ፡ ያቺን መዝሙር እንድንዘምር፡ ወደ መድረኩ ይሰበኝ ነበር፣ "በዚያ የሚጠብቀኝ አለ... " [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ—ኤዲ.]... ? ...

93 የሆነ ነገር ሆነብኝ! ዓለምን አስወገደው። ነገሮችን በተለየ መልኩ ማየት ጀመርኩ። እነዚህ የአሜሪካ ሰዎች በሚያደርጉት ነገር ከዓመት ዓመት፡ በተደጋጋሚ፡ እራሴን አስጨንቄአለሁ፣ ሴቶች እና ወንዶች ሁሉ እራሳቸውን ምን ያህል ከንቱ እያደረጉ እንዳሉ ሳይ፣ ሁለት ሦስት ጊዜ፡ እስክጨነቅ ድረስ፡ በዚህ ጉዳይ ብዙ አሰቤአለሁ። ትላንት ግን፣ እግዚአብሔርን እንዲህ አልኩት፦ "ከእንግዲህ አልጨነቅም። ቃልህ እንዲህ እንደሚሆን ተናግሯል። ነገር ግን በእኔ ውስጥ ካለው ሁሉ ጋር በመጣስ፡እጸናለሁ እቋቋማለሁ አልኩት።"

94 በቀደም ለታ፡ እዚያ በጫካ ውስጥ፡ በዋሻዬ፡ በግሪን ሚል ቆሜ፡ ቀኑን ሙሉ ስጸልይ ዋልኩኝ። እና ወደ ሦስት ሰዓት ሲሆን፣ ፀሐይ እየጠለቀች ነበር፣ እና እዚያ ቆሜ አሻግሬ ሳይ፣ ከዋሻው ወጥቼ፡ ትልቅ ድንጋይ ላይ ነበርኩ። ወደ

ምስራቅ በኩል ዞሬ፡ እዚያው ቆሜ፡ ጌታን እያመሰገንኩ ነበር። ፀሐይ በተራራው እናት ላይ ከዛፎች በስተጀርባ ስትወርድ ትታየኝ ነበር፣ እና ብዙ ቅጠላ ቅጠል የበዙበትን፡ እጅግ ጸጥ ያለውን፡ ማዶ ወደነበረው ገደል አሻግሬ አየሁ። እና እንዲህ አልኩ፦ “ጌታ ሆይ፡ አንድ ቀን ሙሴን በዓለት ንቃቃት ውስጥ ሸሸገህ፡ በአጠገቡ አለፍክ፡ እጅግ ደክሞት ነበርና። አንተ ግን በአጠገቡ አለፍክ፡ እሱም ‘የሰው ጀርባ ይመስላል’ ብሏል።” እኔም፦ “ጌታ ሆይ፡ አለቱ ላይ ሸሽገኝ” አልኩ። በዚያን ጊዜ፣ በአንደኛው ጎኔ በኩል፣ በቁጥቋጦዎቹ ላይ የሚንቀሳቀስ ትንሽ ነፋስ መጣ። ወደ ፊት ተንቀሳቀሰና፡ ወደ ጎኔ መጣ፡ ትንሹ ነፋስ ተንቀሳቅሶ፡ በጫቃዎቹ ውስጥ ወደ ታች ወረደ። እዚያው ቆምኩኝ።

መቼ እና የት እግዚአብሄር ያውቃል፡ አንድ ቀን፣
የሟች ሕይወት መንኮራኩሮች ሁሉም ይቆማሉ፣
በዚያን ጊዜ በጽዮን ተራራ ላይ ለመኖር እሄዳለሁ።

የሟች አእምሮ ከማይደርሰበት አንድ ቀን፣
መቼ እና የት እግዚአብሄር ያውቃል፡ አንድ ቀን፣

ምን ይሆናል? የሚሽከረከሩትን ትናንሽ መንኮራኩሮች ሁሉ፡ ትዘጋጋለች።

የሟች ሕይወት መንኮራኩሮች ሁሉም ይቆማሉ፣
በዚያን ጊዜ በጽዮን ተራራ ላይ ለመኖር እንሄዳለን።

ወረደች፡ ውቢት ሰረገላ፣
መጣች ቤት ልትወስደኝ ብላ፡
ወረደች፡ ውቢት ሰረገላ፣
መጣች ቤት ልትወስደኝ ብላ።

ከ’ኔ በፊት ከደረሳችሁ፣
መጣች ቤት ልትወስደኝ ብላ፡
ወንድም ቦስዎርዝን፡ ጓደኞቼም ሁሉ፡ ንገሯቸው፣
በቃ መጣች ቤት ልትወስደኝ ብላ።

እስኪ አሁን ወረደች... (አንድ ቀን ቁልቁል ትወርዳለች ይዛኝም ትሄዳለች።)... ሰረገላ-...
(ዛፍ ሁሉ ይቃጠላል፣ የእግዚአብሔር መላእክት፣ የእሳት ሰረገላ)... እኔን ወደ ቤት ለመውሰድ፣
ወረደች፡ ውቢት ሰረገላ፣
መጣች ቤት ልትወስደኝ ብላ፡

95 ከነዚህ ቀናት አንዷ ላይ፣ ከእነዚህ ቀናት ውስጥ አንዷ በሞቴ የንጥፍጣፊ ሰዓታት ውስጥ፡ እንዲመጣ እጠብቀውአለሁ። ትክክል።

ዮርዳኖስን ተመለከትኩ ምንስ አየሁ
መጣች ቤት ልትወስደኝ ብላ፡ (የጥንቱ ኤልያስ ዮርዳኖስን እንዳየ)
ብዙ የመላእክት ጉባኤ ከኋላየ መጡ፡
ቤት ልትወስዱኝ ይመጡ ነበርና።

ወረደች፡ ዝቅ አለች፡ ውቢት ሰረገላ፣
መጣች ቤት ልትወሰደኝ ብላ፡
ወረደች፡ ውቢት ሰረገላ፣
መጣች ቤት ልትወሰደኝ ብላ።

96 የተባረከ የዚህች ሠረገላ ነጂ፣ ጌታ ኢየሱስ፣ የጥንቷ የጽዮን መርከብ፡ የሕይወት ጀልባ አብራሪ፣ በህንጻው ውስጥ ወደ ታች በመንቀሳቀስ ይገኛል፣ የእርሱ መገኘት እዚህ አለ፡ እላለሁ። ከመቃብር ያሰነሳው ራሱ መንፈስ ቅዱስ እዚህ አለ።

97 አንድም የጸሎት ካርዶችን ሰላልሰጡ፣ እኔ የማላውቀው፡ ከከተማ ውጪ የመጣ፡ ሊጸልይለት የሚፈልግ ሰው አለ? እኔ የማላውቃችሁ፡ እጆቻችሁ ወደ ላይ አንሱ። የማላውቃቸው እጆች፡ ወደ ላይ ይነሱ። አንተ፡ እዚያ ጋር። እዚያ ጋር ያለው ጺማሙ ሰውየ መሰለኝ፡ በዚያ በኩል፡ ወደዚያ አከባቢ እጅ ተነስቷል። አዎን፡ አንተ፡ እጅህን አውጥተሃል አይደል? መልካም። ጋሼ፡ አንተ፡ ከኋላ ያለኸው። በጣም ጥሩ። ሁላችሁም ለእኔ እንግዳ ናችሁ? የመንጋው እረኛ ጌታ ኢየሱስ እዚህ አለ፣ ተሰፋዎቹ እውነት እንደሆኑ ታምናለህ? ቤተክርስቲያኑን ቀብቷታል፡ “እኔ የማደርገውን ሥራ እናንተም ደግሞ ታደርጋላችሁ። እኔ ወደ አብ እሄዳለሁና ከዚህ የሚበልጥ ታደርጋላችሁ። ከዚህ በላይ!” ይሄን ታምናለህ?

98 እኔን ሰለማታውቀኝ ነህ እጅህን ያነሳኸው? ሴትየዋ ልብሱን እንደነካች ሁሉ እግዚአብሔር በልብህ ውስጥ ያለውን ሊነግረኝ፡ ሊናገረኝ እንደሚችል ታምናለህ? እሱ በድካሞቻችን ሰሜት ሊነካ የሚችል ሊቀ ካህናት እንደሆነ ታምናለህ? እግዚአብሔር ያለህበት ሁኔታ ቢገልጥልኝ፣ እኔ የእሱ ነቢይ እንደሆንኩስ ታምናለህ፣ የእሱ መገኘት እዚህ እንዳለ በዚህም ምክንያት ይህን እንደፈቀደ ታምናለህ? ሰለ ሚሰትህ ትጸልያለህ። ዳሌዋ ተሰብረዋል፣ የተሰበረ ዳሌ አላት። ይህ እውነት ነው። ትክክል ከሆነ፡ ተነሣ። በጣም ጥሩ፡ በል ሂድና፡ ተፈውሳ አግኛት። አሜን።

99 አንተስ ከኋላ ያለኸው፡ የቆምከው ሰውየ፡ ባለ ጢም? በሙሉ ልብህ ታምናለህ? እግዚአብሔር ችግርህን ሊነግረኝ እንደሚችል ታምናለህ? ልጅህ እንደሚድን ታምናለህ? አምነሃል? ሸባ የሆነ፡ ወንድ ልጅ አለህ። ትክክል። አይደለህም... ከኬንታኪ ነህ። ትክክል ከሆነ፡ እጅህን ወደ ላይ አንሣ። እኔ አላውቅህም፡ አውቅሃለሁ እንዴ? ካወቅሁህ... እጅህን **እንዲህ** ከፍ አርግ፡ አንተዋወቅም። ትክክል። በእግዚአብሔር እመን። ታምናለህ? እንደ እምነትህ ልጅህን እንዲሁ አግኝ። በልብህ ላይ ብቻ አኑር።

100 ማን ነበር እጁን ወደ ላይ ያነሳው፣ እኔ የማላውቀው—የማላውቀው... አንተ ነህ? በጣም ጥሩ፡ ጋሼ የእግዚአብሔር ነቢይ እንደሆንኩ፡ ያምናሉ? [ሰውየው፦ “አሜን” አሉ—አርታዒ.] በሙሉ ልብ፡ ታምናለህ? መነሳት አይገባዎትም፣ ልክ እዚያው ይቁሙ። በጣም ጥሩ፡ ጋሼ፡ የአንተ ችግር ምንድነው፡ የሰኳር ህመም አለብህ። እግርህን እያሰቃየህ ነው። ከወደ ኦሃዮ ነህ። ሰምህ አቶ/ ሚለር ይባላል። ወደቤትህ በደህና ተመለሰ። መልካም፡ በሙሉ ልብ እመን። መልካም።

በሙላት ታምናለህ... ? እመን። ካመንክ!

101 እዚህ የተቀመጠሽው እመቤት፣ እጅሽን አውጥተሻል? መነጽር ያጠለቅሽው፡ ትልቋ እመቤት፡ በሙሉ ልብ ታምኚአለሽ? በሙላት ታምኚአለሽ... የእግዚአብሔር አገልጋይ እንደሆንኩ ታምኚአለሽ? አመንሽ? በጣም ጥሩ፡ እግዚአብሄር ችግርሽ ከነገረኝ፡ ታምኚአለሽ? የልብ ህመም። እሺ፡ ትክክል ከሆነ እጅሽን ወደ ላይ አንሺ። እሺ።

102 እዚህ አጠገብሽ ያለችው እመቤት፡ ተነስታለች። ልብ፡ ግን በእርግጥ ዓይኖችሽ ናቸው። አውቃታለሁ። እሺ፡ ማመን ከቻልሽ!

103 ማዶ ላይ፡ ቀጥሎ ያለውን ሰውየ አንተም፡ የልብ ህመም፡ እንዲሁም የቆዳ በሽታ አለብህ። እግዚአብሔር እንደሚፈውሰህ ታምናለህ? አምነሃል፡ ጋሼ?

104 ወደ ኋላ አካባቢ፡ እጆቹን ወደ ላይ ያነሳ ሰው አለ... አቶ/ ሹበርት። በጣም ጥሩ፡ ጋሼ። እሺ፡ ታምናለህ? ያንተም፡ አይንህ ነው፡ አይደለም’ዴ? እንዲሁም፡ እዚያው ለተቀመጡ ለእናትህ እየጸለይክላቸው ነህ። ይህ ልክ ከሆነ፡ እጅህን ከፍ አድርግ። እኛ አንተዋወቅም። ልክ ነው? እጆቻችሁ ተጨባበጡ፡ እያንዳንዳችሁ እጆቻችሁ ተጨባበጡ። በጣም ጥሩ፡ ይሄው ነው። ማመን ከቻላችሁ፡ መቀበል ትችላላችሁ!

105 ከሞት የተነሳው ኢየሱስ ክርስቶስ በህንጻው ውስጥ ነው። እሱ ያው ነው። ምንስ ይጠቅማችኋል? ዓለም ያላችሁን አቅም ሁሉ እንዲያሟጥጥባችሁ ፈቅዳቿል? ክብር! አዲስ ልደትን እፈልጋለሁ! አዲስ ህይወት እሻለሁ! ምን ዓይነት አውሮፕላን ይምጣ ግድ የለኝም፣ የተቀደሰ ተንከባላይ መሆን ካለብኝ፣ የሆነ ይሁን። ምን ዓይነት አውሮፕላን ይምጣ ግድ የለኝም፣ አሁን በእኔ ላይ ያለውን አይነት እውነተኛ መንፈስ ቅዱስ እሻለሁ። ከ’ኔ ጋር ማቆየት እፈልጋለሁ! በዓለም ካለው ሁሉ ይልቅ እሱ ቢኖረኝ እመርጣለሁ። አሜን! ታምናላችሁ? እሱ እዚህ እንዳለ ታምናላችሁ?

106 እንግዲያውስ፡ እጆቻችሁ እርስ በእርሳችሁ ላይ ጫኑ። አንዳች እሱ የሚችላት ነገር ንገሩኝ። ምንም። አሁን እመኑ። እንዳበቃለት እመኑ።

107 ጌታ እግዚአብሔር፣ የሰማይና የምድር ፈጣሪ፣ የዘላለም ሕይወት ደራሲ፣ የመልካም ሰጦታ ሁሉ ሰጪ፣ ጌታ ሆይ፡ ህንጻው ወደፊት ወደኋላ፡ የሚተነፍስ እስኪመስል ድረስ፡ መንፈስህ በብዙ ቅባት እዚህ ተሞልቷል። ጌታ ሆይ፡ ሕዝቡ ለምን ሊገባው አልቻለም? ምናልባት—ከዓለምጋር እጅግ ተዛምደው፡ ቀዝቃዞች እና ተራ እና ግትሮች ስለሆኑ ይሆኑን፣ አንተን ማወቅ እስኪያቅታቸው ድረሰ ሆነው ይሆኑን? ጌታ አምላክ ሆይ፡ ይህ ኃይል ሁሉንም ይንካቸው፡ የታመመ ሁሉ ይፈወስ፡ ሐጥያተኛው ይዳን፡ ለእግዚአብሄርም ክብር ይሁንለት። በእግዚአብሄር ልጅ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ሰም፡ እጸልያለሁ። አሜን።

108 ታምናላችሁ? እጃችሁን ወደ ላይ ከፍ አድርጉ። ፈውሳችሁን ተቀብላችኋል? እግዚአብሔር ይባርካችሁ። አሁን ሂዱና እንዳመናችሁ ይሁንላችሁ፡ እንዲሁ ይሆናል። ራዕዮች በሌሎች ላይ ሲገለጡ ይታየኛል። ትክክል ነው። ዛሬ ማታ መመለስ አለብኝ።

109 አሁን ማመን ካልቻላችሁ፡ ፈጽማችሁ አታምኑም። በትክክል። ኢየሱስም አንድ ቀን እንዲሁ አረገና፡ እንዲህ አሉት፡- “አንተ... መሲሕ ሲመጣ፡ እነዚህን ነገሮች ይነግረናል” አሉት። እንዲህ አለችው፡- “መሲሑ ይሄን እንደሚያደርግ አውቃለሁ። ግን አንተ ማን ነህ? ”

እሱም፡- “እኔ እሱ ነኝ” አላት።

110 ከዚያም ወደ ከተማዋ ሮጣ እንዲህ አለች፣ “ምን እንደሆንኩ እና ያደረግሁትን የሚያውቅ ሰው ኑና እዩ። መሲሕ አይደለምን? ”

111 እሱም፡- “በመጨረሻዎቹ ቀናት እነዚህ ነገሮች እንደገና ይነሣሉ። ቤተክርስትያን እውነት ትሰብካለች፡ በቃሉ ላይ ትቆማለች። የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ሁሉ ትፈጽማለች። ከዓለም ጋር አትገናኝም። ያኔም ቢሆን እሰራለሁ ተመሳሳይ ነገርም አደርጋለሁ አላቸው።”

112 እርሱ ግን፦ “ችኩሎች፡ በትዕቢት የተነፉ፡ ከእግዚአብሔር ይልቅ ተድላን የሚወዱ ይሆናሉ፣ ዕርቅን የማይሰሙ፡ ሐሰተኞች ከሳሾች፡ የአምልኮት መልክ ያላቸው፡” ቤተክርስትያን ሄያጆች፡ በጣም ሃይማኖተኞች። “የአምልኮት መልክ አላቸው፡ ኃይሉን ግን ክደዋል። ከእንደዚህ ዓይነት ራቅ!”

113 እናንተ ሰዎች፣ በቤተክርስቲያኑ ውስጥ በያላችሁበት፣ እሱ አሁን የጠራችሁ፣ ራዕዩ አሁን ከእኔ ተወሰዷል። እኔ ስለእናንተ አንዳች ሳላውቅ፡ ያልኩት ሁሉ፡ እውነት ከ—ከነበረ፡ ማናችሁንም ብትሆኑ እጆቻችሁን ከፍ አድርጉ። በመላው ቤተክርስቲያን፣ እያንዳንዱ—እያንዳንዱ ሰው። በጣም ጥሩ። አያችሁ? አላውቃቸውም፡ አይቻቸው አላውቅም፡ የሚያውቃቸው መንፈስ ቅዱስ ግን እዚሁ አለ። እኔ'ኮ አይደለሁም አይታያችሁም?

114 ሰሙኝ! በዚህ ነገር ላይ እኔን ካመነኝ፡ በቃሉ እውነት ላይም እኔን ያምነኛል፡ ምክንያቱ እውነት የሚመጣው በቃል ብቻ ነው። “ንስሐ ግቡ፣ ለኃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ሰም ተጠመቁ፣ የመንፈስ ቅዱስንም ሰጦታ ትቀበላላችሁ፡ የተሰፋው ቃል ለእናንተና ለልጆቻችሁ፡ ጌታ አምላካችንም ወደ እርሱ፣ ለሚጠራቸው በሩቅ ላሉ ሁሉነውና።” ታምናላችሁ? ከጥቂት ጊዜ በኋላ የጥምቀት አገልግሎት አለ።

115 እንገታችንን ዝቅ እናድርግ። ለጥምቀት ሲዘጋጁ ፓስተሩን እንዲጸልይ እጠይቃለሁ። የጥምቀት አገልግሎት ያለ ይመስለኛል። በጣም ጥሩ።

**በዓለም የተታለለች፡ ቤተክርሰትያን** AMH59-0628M

(A Deceived Church, By The World)

**የቤተክርሰትያኒቱ መተካካት**

ይህ መልዕክት በወንድም ዊልያም ማርዮን ብራንሃም በኢንግሊዘኛ የተላለፈ መልዕክት በ ሰኔ 28፡1959፡ እሁድ ጠዋት፡ ጀፈርሰንቪል፡ ኢንዲያና፡ ዩ.ኤሰ.ኤ.፣ በሚገኘው ብራንሃም ተበርናክል፣ ከማግኔቲክ ቴፕ ቅጂ ተወሰዶ ሳይሸራረፍ ወደ ኢንግሊዘኛ ተጽፏል። ይህ የአማርኛው እትም በቮይሰ ኦቭ ጋድ ሪከርዲንግሰ ተተርጉሞ ተሰራጭቷል።

AMHARIC

©2022 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

VOICE OF GOD RECORDINGS

P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.

www.branham.org

## የቅጂ መብት ማሳሰብያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው።

ተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ከፈልጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡



Voice Of God Recordings
P.O. Box 950, Jeffersonville, Indiana 47131 U.S.A.
www.branham.org